


በመቃድስ ላይ የሚገኘው የቅድስት ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ዋጋው ፩ ብር

# ንሥ



ከቋጥኝ ተፈልፍሎ የተሠራው የቅ·ላሊበላ ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር ፩፻፵፭

የኅዳርና የታኅሣሥ ወራት ፲፱፻፹፫ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ
ም አዘጋጅ መ/ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማውጫ

## አርእስት

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ርእሰ አንቀጽ የሚዘራና የሚያጭድ አብረው ደስ ይላቸዋል ። | ፪ |
| ቅዱስ ሲኖዶስ ዘወርኃ ጥቅምት | ፬ |
| ሰበካ ጉባኤ በሀገረ ስብከት | ፯ |
| ዜና ሊቃውንት | ፱ |
| የቤተ ክርስቲያን ታሪክ | ፲ |
| የሴቶች ዓምድ | ፲፫ |
| ዜና ዕረፍት | ፲፭ |
| መሠረተ ሕይወት ማርያም | ፲፯ |
| የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት በቁልቢ ... | ፲፰ |
| ጸሎተ እሥራኤል | ፲፱ |
| ብርሃን ወደ ዓለም መጣ | ፳፩ |
| ታላቁ የእግዚአብሔር ቀን | ፳፫ |

## ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጆች

በቅድሚያ የእግዚአብሔር ፍቅርና ሰላም ከእናንተ አይለዩ እያልኩኝ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ቀጥየም የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀርባለሁ ።

፩ኛ· በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሜሮንና የቅባ ቅዱስ ልዩነት ምንድነው ነው?

፪ኛ· ዲያቆን ማጥመቅ አይችልም ይባላል ፊልጶስ ግን የኢትዮጵያን ጃንደረባ አጥምቆታል ፤ ይህ እንዴት ነው ?

፫ኛ· አንድ ሕፃን ልጅ ለጥምቀት የተወሰነው ቀን ሳይደርስ ቢጠመቅ መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል ? አያድርበትም ? ሕፃኑስ ሳይጠመቅ ቢሞት ይጸድቃል ? ይኮነናል ?

፬ኛ· አንድ ልጅ የንስሐ አባት መያዝ የሚገባው በስንት ዓመቱ ነው ?

፭ኛ· ወንድ ድንግልናውን ካፈረሰ በኋላ በድንግልና ከኖረች ሴት ጋር ለመጋባት ቢፈልግ በተለይ በድንግልና ለቆየችው ሴት ጸሎተ ተክሊል ሊደረስላት ይችላልን?

፮ኛ· በአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት አልፎ አልፎ ጫማ አድርጎ መግባት የተለመደ ሆኖአል ይህ ተገቢ ነውን?

፯ኛ· አሁንም በአዲስ አበባም ሆነ በሌላ ክፍለ ሀገር በክርስትና ጊዜ እናቶች ውኃ በፔርሙዝ እያሞቁ ይዘው እየመጡ ሕፃኑን ልጅ በዚያ ውኃ አሐዱ አብ ተብሎ ተባርኮ በዚያው እያጠመቁ ይሄዳሉ ይህ ከምን የተገኘ ነው? ለመሆኑ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በሞቀ ውኃ ነው ወይ ?

፰ኛ· እስላም ወይም ከሃዲ ሚስት አግብቶ ከወለደ በኋላ ሚስቱን ፈትቶ ወደ ክርስትና እምነት ተመልሶ ቢጠመቅ ሥልጣነ ክህነት መቀበል ይችላልን?

፱ኛ· በወሎ ክ/ሀገር ከቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ የሚገኙ ሊቃውንት ሲሞቱም ሆነ በሕይወተ ሥጋ እያሉ በትንሣኤ መጽሔት በዜና ሊቃውንት ዓምድ ላይ ታትሞ ሲወጣ አይታይም ሌላው ቀርቶ የቤተ ክርስቲያን ፎቶ ግራፍ በትንሣኤ መጽሔት ሽፋን አይወጣም የሌሎቹ አህጉረ ስብከት ሊቃውንት ታሪክና የቤተ ክርስቲያን ፎቶ እየወጡ የወሎ የማይወጣ ለምንድር ነው?

፲ኛ· በትንሣኤ መጽሔት የሐምሌና የነሐሴ ወራት ፲፱፻፹፪ ዓ/ም በቁጥር ፩፻፵፫ በጥያቄ አምድ ላይ በወህኒ ቤቶች ጽላቶች መኖራቸው ተገልጿል ፤ ነገር ግን በዚያው ወህኒ ቤት በእሥር ላይ የሚገኙ ልዑካን ሊቀድሱ ይችላሉን ከተፈቱስ በኋላ ይቀድሳሉ ወይ ? በተጨማሪም በወህኒ ቤት የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ሀ/ስበከት የቆጣጠራቸዋል?

፲፩ኛ· በዛሬው ጊዜ በርከት ባሉ በኢትዮጵያ ከተሞች የሚሸጡ የእመቤታችን ድንግል ማርያም ሥዕሎች የጆሮ ጉትቻና ለሴቶች የተለያዩ ጌጣ ጌጦች እየተደረጉ እየተሸጡ ናቸው ሻጮችም የኦርቶዶክስ ልጆች ናቸው ይህንን ቤተ ክህነት በምን መልክ ይመለከተዋል ?

እንግዲህ ላቀረብኳቸው ጥያቄዎች ሁሉ መልስ እንደምትሰጡኝ በተስፋ እጠብቃለሁ ። ዲ· በላይ ወርቁ ከደቡብ ወሎ ደሴ ገነተ ጊዮርጊስ ፍሬ ገነት የሰ/ት/ቤት ።

### መልስ

ዲያቆን በላይ ወርቁ ስለአቀረብ ክልን መንፈሳዊ ሰላምታ እኛም በበኩላችን የሰላምታ አጸፋን እየመለስን ለአቀረብካቸው ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ።

በመጀመሪያው ጥያቄህ ስለሜሮንና ቅብዓ ቅዱስ ልዩነት ጠይቀሃል ሁለቱ የሚለያዩት በአወጣጣቸው ነው ሜሮን ከብዙ ዕፀዋት ተሰብስቦ ተጸልዮበት ነው በአገልግሎት ላይ የሚውለው የሚጸልዩበትም ፓትርያርኩ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው ቅብዓ ቅዱስ ግን ዕለታዊ ጸሎት ከተጸለየበት በኋላ በአገልግሎት ላይ ይውላል ።

፪ኛ· ዲያቆን ለማጥመቅ ይችላልን ብለህ ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ማጥመቁን ጠቅሰሃል ዲያቆን ለማጥመቅ አይችልም እንዲያጠምቅ የሚፈቀድለት ቄስ ነው ፤ ፊልጶስ ዲያቆን ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ ትልዎ ለዝ ሠረገላ ያለው ቃል እንደ ቅስና ሹመት ተቆጥሮለት ነው ያጠመቀው ።

፫ኛ· አንድ ሕፃን ለጥምቀት ከተወሰነው ጊዜ ሳይደርስ ቢጠመቅ መንፈስ ቅዱስ ይወርድለታል እንጅ በቀኑ ማነሥና መብዛት መንፈስ ቅዱስ ከመውረድ አይከለክልበትም ። ሳይጠመቅ ቢሞትም የክርስቲያን ልጅ ከሆነ ኩነኔ የለበትም ።

፬ኛ· አንድ ልጅ የንስሐ አባት እንዲኖረው የሚያስፈልገው ከሰባት ዓመት ጀምሮ ነው ይህም ሲባል ሕፃኑ ራሱ ፈልጎ የንስሐ

ወደ ገጽ ፫ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# የሚዘራና የሚያጭድ አብረው ደስ ይላቸዋል

ጠቢቡ ሰሎሞን "ለሁሉም ጊዜ አለው" ብሎ እንደተናገረው የዘርና የመከር ወቅቶች የተለያዩ ናቸው ፤ በግብርና ሥራ ተመድበው የሚሠሩ ገበሬዎች በዘመነ ክረምት ይዘራሉ ፤ በዘመነ መፀው ደግሞ በክረምት የዘሩትን ሰብል ያጭዳሉ ይሰበስባሉ ፤ ይከምራሉ ይወቃሉ ገለባውን ከፍሬው ለይተው በጎተራ ሲያከማቹ ገለባውን በእሳት ያቃጥላሉ በዚህም ሥራቸው ራሳቸውን ችለው በልተው ጠግበው ለሌላውም ይተርፋሉ ።

የመዝሪያ የማጨጃና የመሰብሰቢያ ጊዜያት የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን የሠራተኞችም የዕለት ኑሮ የተለያየ ሁኔታ አለው ። በዘመነ ክረምት እየተቸገሩ ፤ እየተራቡ ያርሳሉ ይዘራሉ በዘመነ መፀው ደግሞ እንደልባቸው እየበሉ እየጠጡ ይሠራሉ ይህንንም ነቢዩ ዳዊት ሲገልጽ "በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ያጭዳሉ ይሰበስባሉ ወደ እርሻቸው በሔዱ ጊዜ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሠማሩ በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ" ብሏል ። መዝ ፻፳፭· ፭—፯ ።

-በዚህ አንጻር ሊቃውንት አባቶቻችን ነቢያትን በክረምት ሐዋርያትን በበጋ ገበሬዎች መስለው ተናግረዋል ። ምሳሌውንም ሲያብራሩ የክረምት ገበሬዎች ጧት ከቤታቸው ሲወጡ ምሳ እያገኙም ሞፈር ቀንበር ፤ ዘርና የበሬ ዕቃዎችን በትከሻቸው ላይ አነባብረው ተሸክመው በሮቻቸውን እየነዱ ወደ እርሻቸው ይሄዳሉ ከዚያም ከላይ ዝናቡ ከታች ጭቃው ወገቦውና ነፋሱ ሲያንገላታቸውና ሲያዋክባቸው ይውላሉ ማታ ወደቤታቸው በተመለሱም ጊዜ የረባ ምግብ አያገኙም ጉመን ጨምቀው በልተው ያድራሉ ክረምት ያለፈው ዘመን እህል የሚያልቅበት የወደፊት አዝመራ የማይደርስበት የቀጠል ጊዜ ነውና በቂ ምግብ ለማግኘት ያስቸግራል ።

የበጋ ገበሬዎች ግን ማለዳ ከቤታቸው ሲወጡ ምሳቸውን በሚገባ በልተው ይወጣሉ ቀን በሥራ በሚውሉበትም ቦታ እሸቱንና እንኩቶውን እየተመገቡ ሲሠሩ ይውላሉ ማታ ወደቤታቸውም ፤ ሲመለሱ እንጀራው በሌማት ጠላው በማቶት ተዘጋጅቶ ይቆያቸዋል ፤ ያንን እየበሉና እየጠጡ ይደሰታሉ ።

በክረምት ገበሬዎች የተመሰሉት ነቢያት ትንቢት በሚናገሩበትና በሚያስተምሩበት ጊዜ ከብሉት ሳይታደሱ በመንፈስ ቅዱስ ሳይጉለምሱ ልጅነትን ሳያገኙ ስለሆነ መከራው ጸንቶባቸዋል ፤ በበጋ ገበሬርት የተመሰሉት ሐዋርያት ግን ፤ በሚያስተምሩበት ጊዜ የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ ከምንም ለይቆጥሩትም ነበር እንዲያውም በአደባባይ አቁመው ወቅሠው ገርፈው ስለክርስቶስ እንዳያስተምሩ አስጠንቅቀው ሲያሰናብቷቸው ደስ እያላቸው ይሄዱ ነበር ። የሐ·ሥራ ም·፭, ፵፩ ።

ነቢያት ስለክርስቶስ ሰው መሆንና ከድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ መወለድ ። ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሰው ሆኖ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት መምረጡን ዓለሙንም በጠቀላላ ከፍዳና ከመርገም ማዳኑን ተናግረዋል ። ምሳሌን መስለዋል ሱባኤንም ቀጥረዋል ። ከተናገሯቸውም ትንቢቶች ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመልከት ።

ከዓበይተ ነቢያት ኢሳይያስ "እነሆ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል ።

እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ለማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ሕፃን ተወለዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና ለለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ። ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም ብሏል ።"
በተጨማሪም ይኸው ነቢይ

"ትወጽእ በትር እምሥርወ ዕሤይ ወየዓርግ ጽጊ እምትንዱ" ከእሤይ ግንድ በትር ትወጣለች ከሥሩም ቁጥቋጦ ያፈራል" ሲል ትንቢት ተናግሯል ኤርምያስም "እርሱም ራሱ ሰው ሁኖ ወደዚህ ዓለም ይገባል ። እኔ ሰው ሆኖ ያየሁት ከባሕርይ አባቱም ወደዚህ ዓለም የመጣ እርሱ ለብሯቸው ይታይ ዘንድ ይገለጥላቸውም ዘንድ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትን ለእርሱ አገልጋዮች ሊሆኑ ይመርጣል ፤ ለማስተማር ወደ ደብረ ዘይት ይወርዳል የተራበችውንም ሰውነት ሁሉ ያጠግባል በማለት ተነብዩአል ።

ሌሎችም ነቢያት ስለክርስቶስ ሰው መሆን ብዙ ምሳሌ መስለዋል ብዙ ሱባኤም ቀጥረዋል ። ብዙ



ትንቢትም ተናግረዋል ነገር ግን ዓረፍተ ዘመን ስለጋረዳቸው ከዘመኑ ሳይደርሱ ሲያልፉ ሐዋርያት ከዘመኑ ደርሰው ከክርስቶስ ተምረዋል ፤ ከእርሱም ጋር አብረው በልተዋል ጠጥተዋል በዓይናቸውም ተመልከተ ዋል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን መርጦ በሚያስተምርበት ጊዜ እነሆ እላችኋለሁ ዓይናችሁን አንሡ ፤ አዝመራውም አሁን እንደደረሰ እርሻውን ተመልከቱ ፤ የሚያጭድ ደመወዝን ይቀበላል ፤ የሚዘራና የሚያጭድም አብረው ደስ እንዲላቸው ለዘለዓለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባሉ አንዱ ይዘራል ፤ አንዱም ያጭዳል የሚለው ቃል ፤ በዚህ እውን ሆኖአልና ፤ እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ ብሏል የዮሐ· ወን· ፬·፴፭—፴፰ ።

እንዲሁም በሉቃስ ወን·፲,፳፫ "እናንተ የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች ብፁዓን ናቸው ። እላችኋለሁና እናንተ የምታዩትን ብዙዎች ነቢያትና ነገሥታት ሊያዩ ወደዱ ለላዩም እናንተ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ወድደው አልሰሙም" በማለት ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሯል "አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው" እንደሚባለው ከልደተ ክርስቶስ በፊት የተነሡት አባቶች ነቢያት የተናገሩት ቃለ ትንቢት በጊዜው የነበሩትን ሐዋርያት ብቻ ሳይሆን ከእነርሱ ቀጥለው የተነሡትን የክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ አስደስቷቸዋል ።

አሁንም ሆነ ወደፊት የሚነሡትና የተነሡት ትውልዶች የሚያስተምሩትና የሚማሩት ስለ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ መወለድና ስለዓለም ድኅነት የተነገሩትን ትንቢታትና የተመሰሉትን ምሳሌዎች የተቆጠሩትን ሱባኤዎች መሠረት በማድረግ ነው ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ

"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጉዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዘመናትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን" ብሏል ።

ነቢያት ትንቢት የተናገሩበት ጊዜ የተለያየ ቢሆንም ትንቢታቱ የሚታወሱበት ወቅት ዘመነ ስብከት ተብሎ ተሠይሟል ይህም ከኅዳር ፲፭ እስከ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ያለው ጊዜ ሲሆን በተለይ ከታኅሣሥ ፯ ፲፫ ቀን ጀምሮ እስከ ልደት ያሉት ሳምንታት ስብከት ፤ ብርሃን ፤ ኖላዊ ፤ እየተባሉ ይጠራሉ ፤ ሐዋርያው "ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ልጁን ላከ" ብሎ እንደገለጸው የትንቢቱ ቀጠሮ በደረሰ ጊዜ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ ተወልዶልናል ገላ ፬·፬

ገበሬ የጣረበት የጋረበት ለብዙ ጊዜ የደከመበት የእርሻ ሰብል ደርሶለት ፍሬውን በተመገበ ጊዜ እንደሚደሰት ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ብለው ያስተማሩለት ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ሐዋርያት በአካለ ሥጋ ተገኝተው ወረደ ተወለደ ብለው አስተምረው ደስ ሲላቸው ይወርዳል ይወለዳል ብለው ያስተማሩ ነቢያትም በአካለ ነፍስ ደስ ተሰኝተዋል የሚዘራና የሚያጭድ አብረው ደስ ይላቸዋል የተባለውም ስለዚህ ነው ። በክርስቶስ ስም አምነን የሐዋርያትን አሠረ ፍኖት ተከትለን የምንማርና የምናስተምር ሁላችንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሰው ሆኖ በመወለዱ ደስ ሊለን ይገባል ።

## ደብዳቤዎች ...

ከገጽ ፩ የዞረ

አባት ይያዝ ማለት አይደለም የወላጆቹ የንስሐ አባት አባቱ መሆኑን አውቆ የሚሠራውን ስሕተት ለንስሐ አባቱ እንዲናዘዝ ማለት ነው ።

፩ኛ· ሴቲቱ ድንግል ወንዱ አግብቶ የፈታ ከሆነ ላላገባችው ድንግል ሴት ጸሎተ ተክሊል እንዲፈጸምላት በፍትሐ ነገሥት ተወ ስኗል ።

፯ኛ· ጫማ ተጫምቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት በቅዱስ መጽሐፍ የተከለከለ ነው ። በሀገራችን ይህ ሥርዓት የተከበረ ሆኖ እስከ አሁን ቆይቷል አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ጫማ አድርገው መግባታቸው ሕግን ተከትለው ሳይሆን ከሕግ ውጭ በሆነ አመለካከት ነው ። ከሕግ ውጭ የሚፈጸም ተግባር ደግሞ እንደ ሕግ ሆኖ መጠቀስ አይኖርበትም ።

፰ኛ· በክርስትና ጊዜ ውኃ አሙቆ አምጥቶ ሕፃን ማስጠመቁ አግባብ አይደለም በክርስቶስ ክርስቲያን የሆነ ሕዝብ መከተል ያለበት ክርስቶስን ነው ጌታችንም የተጠመቀው በፈሳሽ ውኃ እንጂ ውኃውን አሙቆ አይደለም ስለዚህ የሚያጠምቁ ቀሳውስት ይህንን የማይገባ ተግባር ከመፈጸም መጠንቀቅ አለባቸው እንላለን ።

፱ኛ· ኢአማኒ ሚስት አግብቶ ከወለደ በኋላ ሚስቱን ፈቶ ወደ ክርስትና እምነት ገብቶ ቢጠመቅ

ወደ ገጽ ፲፬ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ሲኖዶስ ዘወርኃ ጥቅምት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በአንድ ዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜያት የቤተ ክርስቲያንንገዳይ ያከናውናል ። ከሁለቱም ጊዜያቶች አንደኛው በጥቅምት ወር ይደረጋል ።

የ፲፱፻፹፫/ም ጉባኤም ጥቅምት ፲፪ ቀን ተጀምሮ ተከናውኗል ። ጉባኤው በሚከፈትበት ከላይ በተጠቀሰው ቀን ዋዜማ ከሰዓት በኋላ በ፲ ሰዓት ከ፴ ደቂቃ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሆን መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በደረሱ ጊዜ የካቴድራሉ ደውል ድምፅ ለ፭ ደቂቃ ያህል አስተጋብቷል ልብሰ ተክህኖ ለብሰው የወርቅ መስቀልና ጽንሐሕ የያዙ ልዑካንም በዝማሬ ተቀብለዋቸዋል ።

ቅዱስነታቸው የጉባኤውን መክፈቻ ጸሎት ካደረጉ በኋላ የጸሎቱ ሥነ ሥርዓት እንደተለመደው ተከናውኗል ከዚያም ጸሎተ ወንጌል ቀጥሎ "ተዘከር ማኅበረከ" የሚለው ምስባክ ተሰብኮ "የማቴዎስ ወንጌል ፭፡፲፬—፲፯" በብፁዕ ዶ፡ አቡነ ገሪማ የኢሉባቦርና የጋምቤላ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ተነቧል ። ብፁዕ አቡነ ገሪማ ንባቡን ካሰሙ በኋላ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" የሚለውን ቃል መነሻ በማድረግ የሚከተለውን መንፈሳዊ መልእክት አስተላልፈዋል ።

**የብፁዕ ዶ/አቡነ ገሪማ የኢሉባቦርና የጋምቤላ ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል መንፈሳዊ መልእክት**

ቤተ ክርስቲያናችን በዓመት ሁለት ጊዜያት የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ታደርጋለች ካስፈለገ ከዚህም በላይ ስብሰባ ይደረጋል ።





ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ቅዱስ ሲኖዶሱን ሲመሩ

— በጉባኤው የመክፈቻ ሥነ ሥርዓትም ሥራችን ሁሉ የተቃና እንዲሆን ፤

— በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ የተያዙት ምሕረቱን ፤ ቸርነቱን እንዲያገኙ ፤

— መንገደኞች ሐዋርያት ጉዞአቸው የተሳካ እንዲሆን ፤

— ዝናመ ምሕረቱን በምንፈልግበት ቦታ ሁሉ ያዘንምልን ዘንድ

— የምድር ፍሬንያሳድግ ያውምር ዘንድ ለመከርም ያደርሰው ዘንድ ፤

— የወንዞችን ውሃ እስከልካቸው ይሞላ ዘንድ ምድርንም ደስ ያሰኛት ዘንድ ትልሚንም ያረካው ዘንድ ለዘርና ለመከርም ያደርሰው ዘንድ ፤

— እግዚአብሔርን ስለምትወድ ስለሀገራችን ስለ ኢትዮጵያ መንግሥቷን ያለ ሕመም በሰላም በእውነትም ይጠብቅ ዘንድ ፤

— በቀናች ሃይማኖት ሁነው ያረፉትን የክርስቶስ ወገኖች የሆኑትን ሁሉ የወንዶችንም የቤቶችንም ነፍሳት ኀዘንና ልቅሶ በሌለበት በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብም አጠገብ በመንግሥተ ሰማያት መኖርን ይሰጣቸው ዘንድ ፤

— ለንኡስ ክርስቲያን ኃጢአትን ለማስተስረይ ዳግም ልደት የሚገኝበትን ስርየት በሚገባ እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ ፤

— በሁሉም ያለች ለከበረች ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን አንድነትን ይሰጣት ዘንድ ለሕዝቡም ለምእመናንም አንድነትን ፍቅርን ሰላምን ይሰጣቸው ዘንድ ይህንና ይህን የመሰለ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር አምላካችን ይቀርባል ።

አሁንም በዚያው ዓይነት ጸሎታችንን ወደ እግዚአብሔር አምላካችን በማቅረብ ላይ ነን ።

እግዚአብሔር አምላካችን ምህረቱን ቸርነቱን ለሀገራችን ለወገናችን ለዓለም ሁሉ ሰላሙን እንዲሰጥልን ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር ንጹሕ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ አጥብቆ ዘወትር መጸለይ ይኖርብናል ። ከዚህ የተሻለ ሌላ መፍትሔ የሌለ በመሆኑ ነው።

ከወንጌሉ ምንባብ እንደተረዳነው "እናንት የዓለም ብርሃን ናችሁ" ይላል (ማቴ·፭ ፡ ቁ· ፲፬)

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹ ሐዋርያትን በብርሃን መስሎ መናገሩን ከዚህ እንረዳለን ። የሐዋርያትን በጎ ሥራ ሰዎች አይተውና ተመልክተው እግዚአብሔር አምላክን ያመስግኑ ዘንድ ነው ።"

"ምንም እንኳ ክፉ አድራጊዎች ናቸው ብለው ቢያሟችሁምሁም እግዚአብሔር እኛን ለመጎብኘት በሚመጣበት ቀን አረማውያን መልካም ሥራችሁን በማየታቸው ምክንያት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ በነርሱ መካከል ስትኖሩ መልካም ጠባይ ይኖራችሁ" ይላል (፩ኛ ጴጥ· ፪ ፡ ፲፪)

ሐዋርያት የዓለም ብርሃን የሚሆኑት የእግዚአብሔርን ቃል በመፈጸምና በማስፈጸም ነው ። "ይህም ከሆነ በዚህ በጠማማና በሥርዓተ አልበኛ ትውልድ መካከል ነውርና ተቀፋ የሌለባችሁ ንጹሐን የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ለዓለም ሕዝብ እንደ ከዋክብት ታበራላችሁ" ይላል (ፊልጵ·፪ ቁ· ፲፭)

ሕገ እግዚአብሔር የዓለም ብርሃን ነው ። ለሚፈጽመውም ፍጹም ሕይወትን ይሰጣል ።

"በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት የሚኖሩ ሰዎች ደስ ይበላቸው፤ ትእዛዛቱን የሚጠብቁ በሙሉ ልባቸውም የሚያገለግሉት ደስ ይበላቸው ፤ እንደዚህ የሚያደርጉ ከቶ አይሳሳቱም የሚኖሩትም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ነው..." ይላል (መዝ·፩፻፲፱ ቁ·፩—፫)

የሕግ ባለቤት ጌታ የዓለም ብርሃን ነው ። "በእርሱ ሕይወት ነበረች ፤ ይህች ሕይወትም የሰዎች ብርሃን ነበረች ፤ ብርሃንም በጨለማ ያበራል ፤ ጨለማ ብርሃንን ከቶ አያሸንፈውም" ይልና (ይህ ብርሃን ወደ ዓለም የሚመጣና ለሰው ሁሉ ብርሃንን የሚሰጥ እውነተኛ ብርሃን ነበር" ይላል (የዮሐንስ ወንጌል ፩፡፬—፱)

ይህ ብርሃን መነሻም መድረሻም ስለሆነ ነው ሐዋርያትን እናንት የዓለም ብርሃን ናችሁ ያላቸው ።

በደመ ክርስቶስ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን የፈቃደ እግዚአብሔርና የትእዛዘ እግዚአብሔር አስፈጻሚና አዋጅ ነጋሪ ስለሆነች የዘመን እሩጫ የሰነፎች ግልምጫ የማይሽረውን ቅዱስ ቃሉን በመፈጸም ጠብቃ ትኖራለች ። "ሰማይና ምድር የልፋል ቃሌ ግን አያልፍም ይላል (ማቴ ፳፬ ቁ·፴፭)

የክርስትናው ታሪክ ሲመሠረት ዓለም ይባል የነበረው የቄሣሩ ግዛት ብቻ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ይቻላል ። "ወኮነ በእውነቱ መዋዕል ወፅአ ትእዛዝ እምኀበ አውግስጦስ ቄሣር ከመ ይጽሐፍ ኵሉ ዓለም" (ሉቃ· ፪ቁ·፩)

በዚያ አሮጌ ዓለም በዚያን ጊዜ የነበረው ሕዝብ

፩ኛ· በሙሴ ሕግ የሚመራው

፪ኛ አማልክት አምላኪው

፫ኛ በዘላንነት የሚኖር ነበር ።

እንግዲህ የክርስትናው ታሪክ የተመሠረተው ከዚሁ ሁሉ ወደ ክርስትናው በሚመጣው ሕዝብ ነበር ።

ያ አማልክት አምላኪ የሆነ የቄሣር አገዛዝ የተጫነው ዓለም ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ተውጦ የሚኖር ነበር ። ያንን ጨለማ ዓለም የሚያበሩ ሐዋርያት አስፈልገው ነበር ። ለዚህም ሐዋርያዊ ተልእኮ የሚሆኑ ሰዎች የተገኙት ከገሊላ አውራጃ ከገሊላ ባሕር አካባቢ ነበር ።

ከአንዱ አስቆሮቱ ይሁዳ በቀር ሁሉም የብርሃን ሰጭነታቸውን ሥራ ፈጽመው በሰማዕትነት ያረፉ ናቸው ። ያ ጨለማ ዓለም ሊበራ የቻለው በነዚህ ዓላማቸውን ባወቁ ቁጥራቸው ባነሰ የገሊላ ሰዎች ነበር ።

የክርስትናው ብርሃን በመጀመሪያው ከፈነጠቀባቸው ጥንታውያን አህጉር አንዲቱ ኢትዮጵያ ሀገራችን ናት ።

የክርስትናው ብርሃን በሀገራችን የፈነጠቀው ቅድመ ክርስትና በነበረው በሙሴ ሕግ መደበኛነት ላይ ነበር ።

በዚያ በመጀመሪያው የክርስትና ዘመን ኢትዮጵያ የሕገ ኦሪት አምልኮትን በምኩራበ ኦሪት ይዛ ትገኝ ነበር ።

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ገደማ የክርስትናው ብርሃን በኢትዮጵያ ጐልቶና አይሎ በመታየቱ ምኩራበ ኦሪቱ ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ተለውጦአል ።

ለዚህ ብርሃን ሰጭነት ምክንያት የሆናት ነገደ ጽርአዊ ወይም ጢሮሳዊ የሆነ ማዓርገ ጵጵስናውን ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ከቅዱስ አትናቴዎስ የተቀበለው ቅዱስ ፍሬ ምናጦስ ነበር ።

በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ በአክሱም በአራተኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ገደማ ለመጀመሪያ



www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ማያጠራት ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም የተጀመረው ሥርዓተ ረበናትን በማስወገድ መሆኑ ግልጽ ነው ። ከዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፍሬ ምናጦስን "ከሣቴ ብርሃን ሰላማ" በማለት ሰየመችው ። ይህም ስያሜ የተሰጠው ከበጎ ሥራው አንጻር ነው ።

ከተዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ አብርሃ ወአጽብሃ ድረስ በሥርዓተ ኦሪት የኖር ነው ፤ ከዚያም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ለመቀበል የበቃ ነው የአክሱም ነገሥታት አብርሃ ወአጽብሐ ፈቅደው በላኩት በፍሬምናጦስ መልእክተኛነት እንጂ ከዚያ በፊት ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ትምህርተ ክርስትናን የሰበከ እንዳልነበረ ታሪኩ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ኢትዮጵያ የክርስናውን ብርሃን በፈቃዱ ከማግኘቷ በቀር መሥራች ባለቤት ነኝ የሚል ቢኖር ሀሰተኛ ነው ።

## አድሬስ

በሐዋርያት ሥራ ምዕ ፲፭ ከቁ ፩ ጀምሮ የተጻፈውን የኢየሩሳሌም ጉባኤ ብንመለከት በሐዋርያት ብርሃን ሰጭነት የሆነውን ሁሉ መረዳት እንችላለን ።

አንዳንድ ያልታወቁ የጸሐፍት ፈሪሳውያን ወገኖች የሆኑ ሰዎች ወደ አንጾኪያ ሄደው በሙሴ ሕግ መሠረት የግዘረትን ሥነ ሥርዓት ካልፈጸሙ ድኅነት የማይገኝ መሆኑን በማስተማራቸው በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ችግር መነሣቱንና ይህም ጉዳይ ወደ ሐዋርያት እንዲደርስ በመደረጉ የተነሳው ችግር በሐዋርያት ጉባኤ ብርሃን ሰጭነት መፍትሔ እንዳገኘ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፲፭ ከቁጥር ፳፫ እስከ ፴፭ መረዳት እንችላለን ።

ጉባኤ ሲደረግ የነቢያትን ፣ የሐዋርያትን ፣ የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ጉባዔ የባረከ እግዚአብሔር ጉባኤያችንን ይባርክልን "አቡነ ዘበሰማያት..." የምንለውም ከዚህ በመነሣት ነው ።

ሰው በሥላሴ አርአያና አምሳል ተፈጥሮ በኃጢአት ቢሰናከልም ከጊዜ በኋላ ሙሴ ተወልዶ በኃይለ እግዚአብሔር አድጎ ታቦተ ሕጉን በሴና ተራራ እስከ ተቀበለ ድረስ በእምነት የተጓዙ ቅዱሳን አበውን እግዚአብሔር ቃል በቃል ያነጋግራቸው እንደነበረ የሙሴ መጽሐፍ ይነግረናል ።

እነርሱም አይተውና ተመልክተው የሚመሩበት ሕገ እግዚአብሔር ብርሃን ሳይኖራቸው ለአምላካቸው ይንበረከኩ ስሙንም በመቀደስ መሥዋዕትንም ያቀረቡ ነበር።

ይህ ብርሃን የማይታይበት ጥቅ ጥቅ ያለ የጨለማ ዘመን ሕገ ልቡና በመባል የታወቀ ሲሆን በአጠቃላይ በኦሪት ዘፍጥረት ያለ ታሪክ ሁሉ በጨለማው በሕገ ልቡና ዘመን የተፈጸመ ነው ። ብሉይ ኪዳንም ወደ አራት ሺህ ዘመን የሚጠጋ እድሜ ያለው ሲሆን ይህም በሥነ ጽሑፍ ከተመዘገበ ጀመሮ እስከ ልደተ ክርስቶስ የነበረውም የሕገ ኦሪት ዘመን ሲሆን ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ያለውም ዓመተ ምህረት በሕገ መንጌል የሚመራ መሆኑ የታወቀ ነው ።

ሕገ እግዚአብሔር ያለበት ዘመን ሁሉ የብርሃኑ ነጸብራቅ የተለያየ ደረጃ ይኑረው እንጂ ብርሃን እንዳልተለየው ይታወቃል ።

ኦሪትና ወንጌል መነሻና መድረሻ በመሆን ሁለቱም በአንድ ጥራዝ መጽሐፍ ቅዱስ ተብለው ይጠራሉ ።

"በርግጥ ሳሩ ይደርቃል ፣ አበባውም ይረግፋል ፣ የአምላካችን ቃል ግን በብርሃን ሰጭነት ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል" ይላል (ኢሳ ፵ ቁ ፰)

ስለዚህ

ሀ) በሙሴ ሕግና በነቢያተ እግዚአብሔር ትምህርት

ለ) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገረው ፣

ሐ) ሐዋርያት ባስተማሩት ፣

መ) በሦስቱ ጉባዔያት በተወሰኑት ማለት በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት እየተመሩ ፫፻፲፰ ቅዱሳን አበው በ፫፻፳፭ ዓ/ም በኒቂያ ፣

፩፻፶ ቅዱሳን አበው በ፫፻፹፩ ዓ/ም በቁስጥንጥንያ ፣

፪፻ ቅዱሳን አበው በ፬፻፴፩ ዓ/ም በኤፌሶን ባስተማሩትና በወሰኑት በነዚህም ቅዱሳን አበው ትምህርትና ውሳኔ ጋር የሚተባበሩ በየጊዜው የተነሱት ቅዱሳን አበው በአስተማሩት በሁሉም ያለች ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ብርሃን ሰጭነት ሥራችን ሁሉ የተቃና እንዲሆን የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ይሁንልን ። አሜን ።

የብፁዕ አቡነ ገሪማ መንፈሳዊ መልእክት እንደ አበቃ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ምዕራገ ጸሎት አድርገው በሂዱበት አኳኋን ወደ መንበረ ፕትረካናቸው ተመልሰዋል ።

የዜናው አቅራቢ
ቀሲ ልሣኑ በዛብኅ



# ሰበካ ጉባኤ በሀ/ስብከት

ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ የምትመራው በቃለ ዓዋዲው በተወሰኑት ሕጋግት መሠረት ነው በሕጉም ላይ በሀ/ስብከቱ መንበረ ጵጵስና በዓመት ሦስት ጊዜያት አጠቃላይ ጉባኤ ይደረጋል ይላል በአጠቃላይ ጉባኤውም ላይ የሚገኙት በአውራጃዎችና በወረዳዎች የሚገኙ ሊቃነ ጳጳሳት አባል የኢሉባቦርና ጋምቤላ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የዚህ ጉባኤ ሊቀ መንበር!

የተከበራችሁ የሀገረ ስብከቱ አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ አባላት የየአውራጃዎች ሊቃነ ካህናት የጅማ ከተማ አድባራት አስተዳዳሪዎች የየአውራጃውና የከተማው ሰበካ ጉባኤ የካህናት የምእ



ብፁዕ ዶ/አቡነ ገሪማ በሰበካ ጉባኤ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ውጤት ላሳዩ ሽልማት ሲሰጡ

ካህናትና ሥራው የሚመለከታቸው ሁሉ ናቸው ።

በቃለ ዓዋዲው ውሳኔ መሠረት በጅማ ከተማ የተደረገውን ስብሰባ የሚመለከት የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት አጠናቅሮ ከላከልን ቃላተ ጉባኤ በከፊል ቀጥለን አቅርበነዋል ። ጉባኤው በብፁዕ አቡነ ገሪማ ጸሎት ከተከፈተ በኋላ ሊቀ ትጉሃን ብርሃኑ የሚከተለውን ንግግር አድርገዋል ።

ብፁዕ አባታችን ዶ/ር አቡነ ገሪማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርሲቲያን የቅ/ሲኖዶስ ምናንና የሰንበት ት/ቤት አባላት ለተመልካችነት የታደማችሁ ወገኖች ከሁሉ በላይ ለሰው ልጅ ኑሮ ዋስትናው ሰላም ነው ፤ ሰላም የእግዚአብሔር በረከት ነው ። ልዑል እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ ላይ አድሮ ስለ ሰላም ሲናገር "ትእዛዜን ብትሰማ ኑሮ ሰላምህ እንደወንዝ ጽድቅህም እንደባሕር ሞገድ በሆነ ነበር" ብሏል ሰላም የሚገኘው ነቢዩ እንደተናገረው ትእዛዙንና ሕጉን በመፈጸም ነው ኢትዮጵያ ሀገራችን የክርስትና እምነትን የተቀበለችው ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በአንደኛው መቶ ዓመት ነው ሀገራችን ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አህጉር አንዷ ብትሆንም በሌሎቹ አፍሪካውያን ወንድሞች የደረሰው የቅኝ ገዥነት ግፍና ውርደት አልደረሰባትም በዚህም ጉዞዋ ከባዕድ ያልተቀላቀለ ኢትዮጵያዊ ባህል አላት ፤ በሃይማኖትም በኩል በዘመነ ኦሪት ብሉይ ኪዳንን በዘመነ ሐዲስ ሐዲስ ኪዳንን ተቀብላለች ይህም ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን መላውን የአፍሪካን ሕዝብ የሚያኮራ ነው ኢትዮጵያ ነፃነቷንና አንድነቷን አክብራና አስከብራ የኖረች ለውጭ ወራሪም ሳትንበረከክ በድል አድራጊነት የቆየችውና ያለችው በሃይማኖቷና በታሪኳ እየተከላከለች መሆኑን ታሪክ ጸሐፊዎች ዘግበውታል ።

ሀገራችን ከክርስትና በፊትም ሆነ በኋላ በሥልጣኔና በነፃነት ይልቁንም በፊደልና በሥነ ጽሑፍ ከጥንታውያን ግብጾችና ግሪኮች የምትወዳደር እንደሆነች የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ" በሚለው መጽሐፋቸው ገልጸውታል ።

እንግዲህ ነፃነትን ከእነክብሩ ፤ አንድነትን ከእንጀግንነቱ ሀገርን ከእነ ድንበሩና ከእነፍቅሩ ሃይማኖቱን ከእነባህሉ አስተባብራ ይዛ የቆየች ሀገራችን ኢትዮጵያ የአሁኑም ትውልድ ጀግንነትና ሀገር ወዳድነትን ለታሪክ ለባሕልና ለሃይማኖት ተቆርቋሪነትን ይዞ እንዲያድግ የማስተማርና የማበረታታት ከፍተኛ ኃላፊነት አለባት ስለዚህ በቅርቡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢ



www.ethiopianorthodox.org

ትዮጵያ አቡነ መርቆሬዎስ በተደጋጋሚ ሀገራችን ያለችበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ገልጸዋል ሰላምን በማጣት ገበሬው ከርሻው ነጋዴው ከንግዱ ተማሪው ከትምህርቱ ሌላውም ሠራተኛ ከሥራው ተለይቶ በረኃብ እሳት መለብለቡን ሁላችንም እናውቃለን፣ ለዚህ ሰላም መታጣት ምክንያት የሆነው ጦርነት እንዲያከትም ከውስጥም ከውጭም ለጦርነቱ ገፊት የሚያደርጉት ሁሉ ወደሰላም ውይይት መድረክ እንዲመጡ ቤተ ክርስቲያናችን ያለባትን ድርሻ ፈጽማለች በመፈጸምም ላይ ትገኛለች ።

ሀገራችን በአሁኑ ጊዜ እጅግ አሳሳቢ በሆኑ ውጥረትና ጦርነት ውስጥ ስለምትገኝ ለሀገርም ጉዳይ ከዜጐች የበለጠ የሚያስብ ስለሌለ እያንዳንዱን ዜጋ ራሱን ለሀገሩ መሥዋዕት እስከ ማድረግ መዘጋጀት ይኖርበታል የጦርነቱ ምክንያት ልዩ ልዩ ነው ።

በባዕዳን ተንኮልና ግፊት ኢትዮጵያ ታሪኳን ለማዛባት ክብሯን ለመግፈፍ አንድነቷን ለማናጋት የሚካሄድ ጦርነት ሲሆን ይህ ውርደት የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ውርደት ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያውያን ነው ።

ስለዚህ በዚህ ጉባኤ ከብፁዕ ወቅዱስ አባታችን አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ስለሀገራችን ሰላም የተላለፈውን አባታዊ ቃለ ምዕዳን ከቅዱስ ሲኖዶስና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላም ጉባኤ የተላለፈውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የሚፈለግብንን የዜግነት ግዴታ፣ በዛሬው ዕለት መመልከት ይኖርብናል ።

ከሁሉ አስቀድመን ለሀገራችን ሰላም አንድነት ክብርና ነፃነት እስከአሁን በዜግነታችን በሃይማኖት መሪያችን ምን አስተዋጽኦ አድርገናል? ወደፊትስ ምን ማድረግ አለብን ብለን ተወያይተን ከአንድ ውሳኔ ላይ መድረስ የመጀመሪያው የጉባኤዎችን አጀንዳ ይሆናል ። ምክንያቱም የሀገር ሰላም ከሌለ ቤተ ክርስቲያን ለአማኞቿ የምትሰጠው መንፈሳዊም ሆነ ማኅበራዊ አገልግሎት ሊከናወን አይችልምና በማለት ተናግረዋል ።

ሊቀ ትጉሃን ብርሃኑ መንገሻ ንግግራቸውን በመቀጠል በሀገረ ስብከት በኩል የተደረገውንና የሚደረገውን የሰበካ ጉባኤ እንቅስቃሴ አንድ በአንድ አሥረድተዋል ። ወደ ልማትም ተግባር መለስ ብለው ሲያብራሩ፣

በሀገረ ስብከት ጽ/ቤት የቅርብ ክትትልና ኃላፊነት የሚካሄድው ልማት አንዱ የደብረ መዊዕ መድኃኔ ዓለም የንዋየ ቅድሳት ማደራጃና የካህናት ማሠልጠኛ የጎጆ እንዱስትሪ ነው፣ ይህ የጎጆ እንዱስትሪ ዕድገት እየጨመረ መሄዱ ታውቋል ።

በጎጆ እንዱስትሪው ውስጥ የሚካሄደው የልማት ዓይነት የቤተና የቢሮ መገልገያ የእንጨት ሥራ ውጤት በንዋየ ቅድሳት ቅርጻ ቅርጽ ሥራ የቃጫ ሥራ ዘርፎች በ፲፱፻፹፪ ዓ/ም የበጀት ዓመት ከምርት ውጤት ሽያጭ የተገኘው ገቢ ከፍ ያለ መሆኑን በመግለጽ ለወደፊቱ የበለጠ መሥራት እንደሚጠበቅበት ተናግረዋል በችግኝ ተከላ በመንገድ ሥራ በእርከን ተግባር በከብት ዕርባታ ሀ/ስብከቱ የሚያደርገውን የልማት እንቅስቃሴ አንድ በአንድ ዘርዝረው በሀገረ ስብከቱ ለተሰበሰበው አጠቃላይ ጉባኤ ገልጸዋል በጉባኤውም መጨረሻ በሰበካ ጉባኤ አደረጃጀት ፣ በልማት ወዘተ ብልጫ ላሳዩ ካህናትና የሰበካ ጉባኤ ተመራጮች የተዘጋጀውን ሽልማት በብፁዕ ዶ.አቡነ ገሪማ የኢሉባቦርና የጋምቤላ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ተሰጥቶ በብፁዕነታቸው ቃለ ምዕዳን ጉባኤው የተፈጸመ መሆኑን ዜናው አረጋግጧል ።

ከኢሉባቦርና ጋምቤላ አህጉረ ስበከት ጽ/ቤት



ብፁዕ ዶ.አቡነ ገሪማ ለጉባኤው መመሪያ ሲሰጡ



# ዜና ሊቃውንት

በቅኔ መምህርነታቸው የታወቁት ሊቅ የመሪጌታ ተሠራ አየለ አጭር የሕይወት ታሪክ ፡

መሪጌታ ተሠራ ከአባታቸው ከአቶ አየለ አገኘሁና ከእናታቸው ከወ/ሠራዊት በሽር በሰሜን ወሎ አስተዳደር ላስታ አውራጃ ውስጥ አሽተን ማርያም ደብር በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ተወለዱ ፡

ለትምህርት ሲደርሱ በተወለዱበት (ደብር) ከመሪጌታ ኪዳነ ማርያም ዘንድ ንባብና ዳዊት ጾምገወ ዜማና ቅዳሴ ተምረው ዲያቆን ሁነዋል ። ከዚያም ወደ ደንጊባት ሒደው ከአለቃ መኰንን ዘንድ ድጓና ዝማሬ መዋሥዕት ምዕራፍ አጠናቀው ተምረዋል ። ከዚህ በኋላ ወደ እየላ ቅዱስ ሚካኤል ሒደው በቅኔ መምህርነት ከታወቁት ከአለቃ ቀጸላ ዘንድ ቅኔ ከነአገባቡ በሚገባ ተምረው በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል።

ሊቁ መሪጌታ ተሠራ የተማሩት ይበቃኛል ሳይሉ ወደ ደብረ ዘመዶ ማርያም ገዳም ሒደው በቅኔ መምህርነት ከታወቁት ሊቅ ከመጋቢ ድሜጥሮስ ዘንድ ከል ሰው ዕርባ ቅምሩንና አገባቡን በማጠናቀቅ በቅኔ መምህርነት ድጋሚ ተመርቀዋል ። ከዚያም ወደ ዋግ ሰቆጣ ሒደው ከአለቃ ዓለሙ ገብሩ ዘንድ አቋቋም በሚገባ ተምረዋል በወይብላ ማርያም ደብር ዋግ ስዩም ከበደ ቅዳሴ ሲያስቀድሱ መሪጌታ ተሠራ ሲቀኙ ሰምተው ሊቃውንቱን ምነው ይህን የመሰለ መልካም ቅኔ አዋቂውን ሳታስተዋውቁኝ አኳቸው ሊቃውንቱም ጌታችን የሚአውቁት መስሎን ነው እንጂ መች ዝም እንል ነበር አሁንም በዚህ በዋግ ስዩም ከተማ በቅኔ መምህርነት ተመድቦ ቢያስተ



መሪጌታ ተሠራ እኒህ ነበሩ

ምር በጣም ጥሩ ነውና ደስ ይለናል የከቡርነትዎ ፈቃድ ይሁንልን ብለው ዋግ ስዩም ከበደን ጠየቋቸው ዋግ ሥዩም ከበደም መልካም ፈቃዳቸው ሁኖ ሠርከ ኅብስት ድርጐና የዓመት ልብስ ደመወዝ ጭምር ፈቅደውላቸው በዋግ ሰቆጣ ከተማ በወይብላ ማርያም ደብር በመምህራን ቤት ሁነው ተወዳጅ ቅኔአቸውን ያስተምሩ ጀመር ።

ሊቁ መሪጌታ ተሠራ ለተማሮቻቸውም ሆነ በቅኔ ማኅሌት የሚዘርፉትና የሚቀኙት ቅኔ ምሥጢሩ እጅግ የሚያስደንቅ መሆኑንም የዋግ ሰቆጣ የቢሮ ሠራተኞችና መኳንንቱ ስለተመለከቱ በትርፍ ጊዜያቸው ወደ መሪጌታ ተሠራ እየሔዱ ተመዝግበው ቅኔ ይማሩ ጀመር የዋግ ስዩም ከበደ ልጅ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደና እንደራሴያቸው ዓለማየሁ ጭምር ሳይቀሩ ከመሪጌታ ተሠራ ቅኔ ለመማር ትምህርት ጀመሩ ፡

ሊቁ መሪጌታ ተሠራም ተግተው ሌሊትና ቀን በማስተማር በ፮ ወር ውስጥ በሚገባ ሁሉንም ቅኔ አስቀኟቸው ከደጃዝማች ኃይሉ ከበደና ከደጃዝማች ዓለማየሁ ጋር ፳፯ መኳንንቶችን ቅኔ አስተምረው አስቀኝተዋል ። ከዋግ ሰቆጣ ከተማ አድባራት ፴ ካህናትን ቅኔ አስቀኝተዋል ። ከእነርሱም ሰባት ካህናትን በመምህርነት መርቀዋል ። ጠቅላላ በዋግ ሰቆጣ ከተማ ፳፰ ዓመት በቅኔ መምህርነት ወንበር ዘርግተው አስተምረዋል ።

ዋግ ስዩም ከበደም ለመሪጌታ ተሠራ ሁለት ጊዜ ጥንግ ድርብና ካባ ከነቀሚሱ ሸልመዋቸዋል ፡ ከንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክም ካባ ከነቀሚሱ ከአባ ደበሎ የብር መቋሚያና ጸናጽል ።

ከቀድሞው ንጉሥ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ካባ ከነጥግ ድርቡ ጋር ተሸልመዋል ።

ሊቁ መሪጌታ ተሠራ በዋግ ሰቆጣ ፳፰ ዓመት በመምህርነት ሲኖሩ አስተምረው ለቅኔ መምህርነት ያበቋቸው ፴፯ ናቸው ።

ከዚህ በኋላ በታላቅ አባትነታቸው በመንግሥትና በቤተ ክህነት የታወቁት አባ ደበሎ የተባሉ አባት መሪጌታ ተሠራ ወደተወለዱበት ቦታ ሒደው የተለመደ የቅኔ ማስተማሩን ተግባር ቢቀጥሉ መልካም ነው ብለው መክረውና ለምነው ለዋግ ስዩም አስፈቅደው ወደተወለዱባት ደብር እንዲመለሱ አደረጉ ተመልሰው በሕግ



www.ethiopianorthodox.org

ሚስት አግብተው አንድ ወንድ ሁለት ሴቶች ልጆችን ወልደዋል በተጨማሪ በቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ደብር በቅኔ መምህርነት ተመድበው የእሸተን ማርያምን መሪጌትነት ደርበው ይዘው ብዙ ቁም ነገሮችን ፈጽመዋል ፤ ብዙ ደቀ መዛሙርትንም ቅኔ አስተምረው ለቁም ነገር አብቅተዋል ፤

ጠቅላላ በቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ፲ ዓመት ቅኔ አስተምረዋል ። ከዚያም የቅዱስ ላሊበላ የ፲፩ ቤተ መቅደሶች የመዘምራን ርእሰ መሪጌታ ሁነው ደክመው ከቤት እስከ ሚውሉ ድረስ በሚገባ ከምስጋና ጋር አገልግለዋል ። ከሁለት መምሀራንም ካባ ተሸልመዋል ፤ የዜማና የቅኔ መጻሕፍቶቻቸውን ለእሸተን ማርያም አስረክበዋል (አውርሰዋል)

ለግብፃዊ ገብረ መንፈስ ቅዱስና ለደረዋ ማርያም ለቤተ አንበሳ ማርያም ካባዎቻቸውን ሰጥተዋል። በመጨረሻም መንኩሰው ቁም ተዝካራቸውን አውጥተው በጾም በጸሎት እንደተወሰኑ በቁመናቸው የመቃብር ቤታቸውን አሠርተዋል ። ከዚህ በኋላ ይህን ሁሉ መንፈሳዊ ትሩፋታቸውን ፈጽመው ከማይቀረው ሞት በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ነሐሴ ፲፱ ቀን በ፹፬ ዓመታቸው አርፈው በቅዱስ ላሊበላ ደብር በታላቅ ማዕረግ የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ።

የዜናው አቅራቢ አባ
ገብረ መስቀል ተስፋዬ
ዘገነተ ማርያም

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## የመስቀል ጦርነቶች በተካሄዱበት ዘመን

## የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የነበረችበት ሁኔታ

ከመ/ሉሌ መልአኩ

ሳራካኖችና ቱርኮች በአሥራ አንደኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ፍልስጥኤምንና ሌሎችንም ሀገሮች በጦርነት ስለያዙ ፤ እዚያው የነበሩትን ክርስቲያኖች በማሠቃየት ብቻ ሳይወሰኑ ወደ ኢየሩሳሌም ለስግደት የሚሄዱትንም ክርስቲያኖች መዝረፍና መግደል ጀመሩ ። ይህንንም አሰቃቂ አድራጎት ዳግማዊ ኡርባን የተባለው የሮሙ ፓፓ ስለሰማ በ፩ሺ፺፭ ዓ.ም ክሌርሞንት ውስጥ ሲኖዶስ አድርጎ ፍልስጥኤምን ከእስላሞች እጅ ነጻ ለማውጣት ወሰነ ። በዚሁ ውሳኔ መሠረት ለዚህ ቅዱስ ዓላማ ለመዋጋት የአውሮፓ ነገሥታትና ሕዝብ ፈቃደኞች ሆኑ ።

በዚሁ መሠረት የመስቀል ጦርነት በተካሄደበትና በአሥራ አንደኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ላይ ኢየሩሳሌም ውስጥ የላቲን መንግሥት በተመሠረተበት ግብጽን ይገዙ የነበሩት የፋቲሚድ (የፋጡማ) ዳይናስቲ ዘሮች የሺዓት እስልምና እምነት ተከታዮች እነ ዋዚር አል አፍዳል ነበሩ ከአል ሐኪም ዕረፍት በኋላ የፋቲማድ ዘሮች ምንም እንኳ በኮፕቶች ላይ ከባድ ሥቃይ የማድረስ ፍላጎት ባይኖራቸውም ፤ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበረው የግብጽ ሕዝብ ከኮፕቶች ጥቂቶቹ በታክስ (በግብር) ሰብሳቢነትና በተለያዩ ሥራዎች ላይ ተሠማርተው ብዙ ሀብት በማፍራታቸው ከፍተኛ ቅናትና ጥላቻ ስላደረበት ሀብታቸውን በኃይል ለመዝረፍ ከመሞከር አልተቆጠበም ነበር ። ያንን ለጥፋት ያሰፈሰፈ ሕዝብ በክርስቲያኖች ላይ ለመፈጸም ከተነሣሣለት የዘረፋ ተግባር ለመግታት መሪዎቹ ስላልቻሉ ያንኑ ሕዝብ ለማስደሰት በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ይሠሩ የነበሩትን ኮፕቶች ያለምንም ጥፋት ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ አባረሩአቸው ።

በኮፕት ፓትርያርኮች ላይ የሚደርሰው እስራትና ሥቃይ ሁል ጊዜ ከእስላሞች በሚሰነዘረው ውንጀላ ብቻ ሳይሆን ፤ አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ ምቀኝነት ቅናት ከሰፈነባቸው በኮፕት መነኩሳትና ጳጳሳት ለገዥዎች በሚቀርበው የሀሰት ውንጀላም ጭምር ነበር ። ለምሳሌ የማዕርግ እድገት ስለተከለከለ ኮሎቶስ የተባለው መነኩሴ በፓትርያርኩ በአቡነ ክርስቶዱሎስ (፩ሺ፵፯—፩ሺ፸፯) ላይ በቀረበው የሀሰት ክስ ምክንያት ባለሥልጣኖቹ የክሱን ይዘት በሚገባ ሳያጣሩ “ሲሻኝ ጢስ ወጋኝ” እንዲሉ ፓትርያርኩን ። አስረው ፣ቤተ ክርስቲያኒቱን ሀብት ወሰዱ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ኮፕቶች ገደብ የለሽ ግብርና የነፍስ ወከፍ ታክስ በመክፈል ፤ አልፎ አልፎም የሚደርሱባቸውን ሥቃዮች በመቀበል የሚያሳልፉት ኑሮ እንሶአቸው የመስቀል ጦርነት ሲጀመር እስላሞች ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ በተዋሕዶ ችና (በኮፕቶችና) በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተፈጠረውን የማይታረቅ ቅራኔና የከረረ ልዩነት ባለመገንዘብ ኮፕቶችን በክርስትና እምነት መሰሎቻቸው ለሆኑት ምዕራባውያን (ካቶሊካውያን) ለመስቀል ጦረኞች በማድላት ውስጥ ውስጡን ያግዛሉ ብለው በመጠራጠር በዓይነ መዓት ይመለከቷቸው ነበር ። ስለዚህ እስላሞች ጦርነቱ የመስቀል ጦርነት እስከሆነ ድረስ የላቲንም (የካቶሊክም) ሆኑ የግሪክ ኦርቶዶክስ ወይም የኮፕቶች ክርስቲያኖች መስቀልን ስለሚቀበሉ ሁሉንም እንደ ደመኛ ጠላት ይመለከቱ ጀመር ። በሌላው ወገን የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ የመስቀል ጦረኞች የተዋሕዶ እምነት ተከታይ ክርስቲያኖች ሁሉ ከሐዲዎች ናቸው ፤ የግሪክ ኦርቶዶክስ ተከታዮች ደግሞ ተገንጣዮች ናቸው በማለት እስላሞችን ድል እያደረጉ በያዙአቸው ሀገሮች በሚኖሩ የተዋሕዶና የግሪክ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ላይ ሥቃይ ፤ የንብረት ጥፋትና ብዝበዛ አድርሰዋል ። በኮፕት ክርስቲያኖች ዘንድ የነበረው ሌላው ችግር ደግሞ አንድ ፓትርያርክ ከሞተ በኋላ ሌላ መርጦ ለመተካት ከገዥዎች ፈቃድ ሲጠየቅ የሚሰጠው ገደብ የለሽ የገንዘብ ክፍያ ነበር ።ለምሳሌ የኮፕት ፓትርያርክ ዳግማዊ መቃርዮስ በ፩ሺ፩፻፳፰ ዓ.ም ከዐረፈ በኋላ ኮፕቶች አዲስ ፓትርያርክ መርጠው ለመሾም ፈቃድ ሲጠይቁ በቅድሚያ ስድስት ሺህ ያህል ዲናር ለመንግሥት ግምጃ ቤት ክፈሉ ተባሉ ኮፕቶችም ለዓመት ግብርና ለነፍስ ወከፍ ታክስ ከሚከፍሉት በተጨማሪ እላይ የተጠቀሰውን ገንዘብ መክፈሉ በጣም ከብዷቸው ሳለ የባሰውን ይባስ ብሎ አንዳንድ ነገር አመላላሾች ኮፕቶች ለቤተ ክርስቲያናቸው መተዳደሪያ ከምእመናን የሚሰበሰቡትን ገንዘብ ለጠላቶቻችን ለፍራንኮች በድብቅ በመላክ ላይ ናቸው በማለት ስላሳበቁ ከሊፋዎች ጉዳዩን በሚገባ ሳያጣሩ ወዲያውኑ አብያተ ክርስቲያናቱ እንዲወረሱ በማዘዛቸው ያለ የሌለው ቅርሳቸው ሙጥጥ ተደርጐ ተወሰደ ። እንዲሁም ፓትርያርክ መርጦ የመሾም ዓላማቸው ተገትቶ ከቆዩ በኋላ በብዙ ደጅ ጥናት ዋዚር አሕመድ ስለፈቀደ ተገቢው ገንዘብ ተከፍሎ አቡነ ገብርኤል (፩ሺ፩፻፴፩—፩ሺ፩፻፵፭) የኮፕት (የእስክንድርያ) ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ ።

የግብጽ ገዥ የነበረው የሱኒ እስልምና እምነት ተከታይ ሳላዲን የአስተዳደር ሥራውን እንደ ጀመረ ኮፕቶችን ከተለያዩ የሥራ ቦታዎች አባረረ ። ከሥራ ገበታቸው በማባረር ብቻ ሳይወሰን ክርስቲያኖች ሁሉ የውርደት ምልክት የሆነ የተለየ ልብስ እንዲለብሱ ፤ ፈረስ እንዳይጋልቡና ከፍ ያለ መቀጫ ገንዘብ ለመንግሥት እንዲከፍሉ አዘዘ ። ኮፕቶችም በግፍ የተጣለባቸውን ገንዘብ ለመክፈል ያለ የሌለ ሀብታቸውን ሸጡ ፤ እርስታቸውንም ለእስላሞች በመሸጥ ርስት የለሽ ሆኑ ። አንዳንዶቹም የእስልምናን እምነት በመቀበል እላይ ከተጠቀሱት ጭቆናዎችና እዳዎች ነጻ ሆኑ ።

እንዲሁም እስክንድርያ ውስጥ ካውካሊስ በተባለው በግብጽ የመጀመሪያውና ጥንታዊው ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ በነበረበት ቦታ ላይ ከእስክንድርያው ፓትርያርክ በአቡነ አጋቶስ (፯፻፷፪—፯፻፹) የተሠራውን ታላቁን የቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል ከሚዲትራንያን ባሕር ወደብ አጠገብ ስለሆነ የመስቀል ጦረኞች በመርከብ ተጉዘው ድንገት እስክንድርያን የያዙ እንደሆነ ምሽግ ያደርጉታል ። በሚል ሰበብ የሰላዲን ሹማምንት ለማፍረስ ከወሰኑ በኋላ ኮፕቶች ባለሥልጣኖችን በመለመንና ሁለት ሺህ ያህል ዲናር በመክፈል ከመፍረስ አድነውታል ።

ሳላዲን በ፩ሺ፩፻፸፫ ዓ.ም ክርስቲያኑን የኑብያን መንግሥት የሚወር ሠራዊት ልኮ በኑብያ ኑአሪዎች ላይ ከባድ ጥፋት አደረገ ። ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ፈረሱ ። የተዋሕዶ እምነት ተከታይ ከሆኑ ጳጳሳት ፤ ካህናትና ምእመናን ብዙዎች ታሠሩ አንዳንዶቹም ለዐረብ የባሪያ ገበያ ለሽያጭ ቀርበው ተቸበቸቡ ። ሆኖም በ፩ሺ፩፻፹፯ ዓ.ም ስላዲን የመስቀል ጦረኞችን ድል አድርጎ ኢየሩሳሌምን ከያዘ በኋላ እሱና ተከታዮቹ በኮፕቶች ላይ የነበራቸውን ጥላቻ ትተው በደኅና ዐይን ይመለከቷቸው ጀመር ። ለጥቂቶቹም ቀደም ሲል የተወሰደው የሥራ ቦታቸው ተመለሰላቸው ። ለሌሎችም ሀብታቸው ተመለሰላቸው ።

በ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን የኮፕቶች መከራና ሥቃይ እንደገና እየጨመረና እየከፋ ሄደ ። ይኸውም በ፩ሺ፪፻፲፱ ዓ.ም እስክንድርያን የያዙ የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ የመስቀል ጦረኞች ምንም ልዩነት ሳያደርጉ ታላቅ ጭካኔ በተሞላበት መንፈስ እስላሞችን ፤ ኮፕቶችንና መለካውያንን መዘበሩ ።

እስላሞችም በበኩላቸው በጭካኔ የሚዋጉንና የሚበዘብዙን የእ





www.ethiopianorthodox.org

ምነት መስሎቻችሁ የመስቀል ጦረኞች ስለሆኑ የደረሰብንን ጉዳት በእናንተ ላይ እንወጣለን በማለት የእስላም ባለስልጣኖች በእስክንድርያው ፓትርያርክ በአቡነ ዮሐንስ ዐሥረኛና (፩ሺ፫፻፳፫—፩ሺ፫፻፳፱) በኮፕቶች ላይ ከፍ ያለ ሥቃይ አድርሰዋል ። የመንበረ ፓትርያርኩንና የቤተ ክርስቲያኒቱንም ሀብት ወርሰዋል ።

ሆኖም ከግብጽ ግዛት ከሦስት አቅጣጫዎች (ሀገር መሪዎች) ለግብጽ ገዥዎች በምልጃና በማስፈራራት መልክ በቀረቡ ጥያቄዎች ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን (ምእመናን) ሰላምና እፎይታን ልታገኝ ችላለች ሦስቱ ምልጃዎችም የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ የቁስጥንጥንያ ንጉሠ ነገሥት ራሱ ከኦቶማን ቱርኮች ጋር በመዋጋት ላይ የነበረ ቢሆንም ግብጽ የሚኖሩትን መለካውያን እንዳያሰቃዩአቸው ለማምሉኮች ዳይናስቲ ያቀረበው ልመና ፤

፪ኛ/ ከግብጽ መንግሥት ጋር መልካም ግንኙነት የነበረው የአራጎን ንጉሥ በግብጽና በኢየሩሳሌም የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት ተከፍተው ለምእመናን መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እንዲሰጡ በማለት ለማምሉኮች ያቀረበው ምልጃ ።

፫ኛ/ ከላይ ከተጠቀሱት ከሁለቱም ጥያቄዎች ከበድ ያለው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በተዋሕዶ እምነት መሰሎቹ በሆኑት በኮፕቶች ላይ የሚፈጸመው ሥቃይ እንዲቆም ፤ የግብጽ እስላሞች በኮፕቶች ላይ የግፍ ተግባራቸውን የሚቀጥሉ ከሆነ እሱም የዐባይን ወንዝ አቅጣጫ በመለወጥና

## ደብዳቤዎች ...

ከገጽ ፫ የዞረ

ሥልጣነ ክህነት ለመቀበል ይችላልን? ስላልከሙ አወን ከእመነና ከተጠመቀ ሥልጣነ ክህነት ቢቀበል የሚከለክለው ነገር አይኖ

---

የተለያዩ ተጽእኖዎችን በማድረግ የሚበቀል መሆኑን ከግብጽ ባለሥልጣኖች ጋር ያደረገው ድርድርና ያስተላለፈው መልእክት ነው።

በ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን ፍሎሬንስ ውስጥ በተደረገችው የፌራራ ሲኖዶስ (፩ሺ፬፻፴፰—፩ሺ፬፻፴፱) የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከኮፕት፡ ከኢትዮጵያ ከግሪክ ኦርቶዶክስ ወዘተ አብያተ ክርስቲያናት ጋር የእርቅ ድርድር ለማድረግ ሞክራ ነበር ። ይኸውም ከተለያዩ የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የተወከሉ ካህናት ፤ እንዲሁም ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ እንጦንስ ገዳም አበምኔት አባ ዮሐንስና ኢየሩሳሌም ካለው የኢትዮጵያ ገዳም ኢትዮጵያዊው አባ ጴጥሮስ ተወክለው በጉባኤው ላይ በመገኘት ውይይት ተጀምሮ ሦስቱንም አብያተ ክርስቲያናት ከሮሙ ፓፓ ሥር ለማድረግ ከእስላሞች ወረራ እና ድናችኋለን በሚል ሽፋን የታቀደ ደባ ስለነበር ግቡን ሳይመታ ቀረ። የጉባኤው አለመሳካት ዋናው ምክንያት የካቶሊክ የግሪክ ኦርቶዶክስና የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ቀደም ሲል ተወጋግዘው የተለያዩባቸውን የእምነት ልዩነቶች አስወግዶ የሚያስማማ በሦስቱም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል መፍትሔ ባለመገኘቱ ነበር ።

ርም።

፱ኛ· በወሎ ሀ/ስብከት የሚገኙ ሊቃውንት ሲሞቱ የሕይወት ታሪካቸው በትንሣኤ መጽሔት በዜና ሊቃውንት ዓምድ አይወጣም በሽፋኑም ላይ ከወሎ አብያተ ክርስቲያናት አይታተምም የሌላው ሀ/ስብከት እየወጣ ለምን የወሎ ሀ/ስብከት አይጣም? በማለት ያቀረብከው ጥያቄ መጽሔቱን አለመመልከትህን ቁልጭ አድርጎ የሚያስረዳ ነው ። አለቃ ጌራ ከልካይ ወ/ሎ ሀ·ስብከት ናቸው እንዲሁም መሪጌታ አስፋው መኮንን በዚሁ ሀገረ ስብከት በራያና ቆቦ አውራጃ የሚገኙ ምሁር ናቸው ። በሞትም የተለዩ ሊቃውንት ታሪካቸው ተጽፎ ወጥቷል ።

በአብያተ ክርስቲያናቱም የእነተ ድባበ ማርያም የእንቅዱስ ላሊበላ የእነ አቡነ አሮን የእነግሸን ቤተ ክርስቲያን በመጽሔቱ ሽፋን ወጥተዋል ። ወደፊትም ቢሆን የአብያተ ክርስቲያናቱን ፎቶ እያነሣ ከእነታሪካቸው ለሚያመጣልን በቅደም ተከተል እያሳተመን ማውጣታችን እና ቋርጥም ግን ሳያነቡ በይሆናል ለምን ይህ አልሆነም ተብሎ ለሚጠየቀው ጥያቄ መልስ ከመስጠት እንታገሣለን ።

፲ኛ· በወህኒ ቤት በእሥር ላይ የሚገኙ ልዑካን እንዲቀድሱ አይፈቀድላቸውም ከተፈቱም በኋላ በዕርግጥ ለታሠሩበት ወንጀል አድራጊዎች ሁነው ተገኝተው ከተፈረደባቸው ከእሥር ቤትም ከወጡ በኋላ ሊቀድሱ አይችሉም የወንጀሉ ሁኔታ ታይቶ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ይሰጠዋል ።

ዲያቆን በላይ ወርቁ በጥያቄህ መጨረሻ የእመቤታችን ሥዕሎች በጌጣ ጌጥ መልክ እየተዘጋጁ ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች መሸጣቸውን



## የሴቶች ዓምድ

# የሴቶችተሳትፎ በሰበካ ጉባኤ

ተሳትፎ ማለት ጾታ ሳይለዩ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደአንድ ቃል ተናጋሪ እየሆኑ ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ሥራ አንድ ሆኖ ተባብሮ መሥራት ማለት ነው ። ሰበካ ጉባኤ ማለት ደግሞ "ወደወንዝ ከመውረድ ይልቅ ወንዙን ወደእንተ አምጣው" በሚለው በፍልስፍና ቃል መሠረት ቤተ ክርስቲያንን ወደሕዝብ ሕዝብን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያመጣ ስለቤተ ክርስቲያን እድገት ስለወንጌል መስፋፋት ፤ የካህናት ኑሮ እንዲሻሻል የሚያደርግ ታላቅ የመገናኛ ድልድይ ነው። ይህ ዕድል በዘመነ ኦሪት ለነበሩት ሴቶች ሳያጋጥማቸው አልፏል ።

ሰሎሞን "ለመትከል ጊዜ አለው የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ አለው" ባለው መሠረት በኦሪት የነበሩ ሴቶች የሚሰጡት አገልግሎት ኅቡዕ እንጂ ይፋ ባለመ

---

ጠቅሰህ ቤተ ክህነት በምን መልክ እንደሚመለከተው ጠይቀሃል ፤

የእመቤታችን ፍቅር ያደረባቸው ምእመናን በፈለጉት ዓይነት እያዘጋጁ የእመቤታችን ሥዕል ቢይዚት መከልከል አስፈላጊ መስሎ ስለማይታይ ቤተ ክህነት በክፉ ዓይን አልተመለከተውም ። በዚህ አጋጣሚ ለተጠቃሚዎች የምናሳስበው በእመቤታችን ድንግል ማርያም ሥዕል መልክ የተቀረፁ ጌጣጌጦች በክብር ተጠብቀው መያዝ እንዳለባቸው ነው ።

ሆኑ ለእግዚአብሔር ከአሥር አንድ እንኳ እንዲከፈል በተወሰነው ጉባኤ ተሳትፎ አልነበራቸውም ።

በዘሌ ም ፳፯ ቁ ፴፪—፴፭ እንደታዘዘው "ምድር ከሰጠችው ከአሥር አንድ የወጣ ሁሉ ከበግም ከፍየልም አሥረኛው ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሁን "ሙሴ ቢልም ለወንዶች እንጂ ለሴቶች ይህ እድል እንዳልተሰጣቸው እና ወንዶች ሲቆጠሩ ሴቶችና ልጆች ከወንዶች ጋር ይቆጠሩ እንዳልነበር ከታሪክ ለመረዳት ይቻላል ።

በዘመነ ሐዲስ ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በሚመላለስበት ጊዜ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩል የመቆጠርና እንደወንዶችም ተከተለው አብረው ያገለግሉና የሥራውም ተካፋይ እንደነበሩ በገንዘባቸውም ጭምር ያገለግሉ እንደነበር ወንጌላዊው ሉቃስ ጽፏል ሉቃ ፰ ፤ ፩—፫)

በመሆኑም ሐዋርያት ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ሰበካ ጉባኤ እንዲቋቋም ማኅበር በጀመሩበት ወቅት ሀብታቸውንና ንብረታቸውን በመስጠት የሰበካ ጉባኤውና የስብከተ ወንጌሉ ተሳታፊ እንደነበሩ የሐ.ሥራ ም ፪ ቁ ፴፪—፴፯ መመልከት ይቻላል በይበልጥም የማርቆስ እናት ማርያም የሥጋ ብቻ ሣይሆን የመንፈስ ሀብታም ስለነበረች ለተቋቋመው መንፈሳዊ ማኅበር ቤቷን ከነሙሉ ድርጅቱ እንዳበረከተች ሀብቷንና ንብረቷን ብቻም ሣይሆን ሕይወቷንም መስዋዕት አድርጋ እንዳቀረበች ከሕይወት ታሪኳ መረዳት ይቻላል ።

በዘመነ ሐዲስ የነበሩ ሴቶች ይህን የመሰለ ታሪክ ሠርተው የሕይወታቸውን ዘመን ለእግዚአብሔርና ለሕዝብ የተቀደሰ አገልግሎት በማበርከት አልፈዋል ። ከዚያ ወዲህ ባለፉት ዘመናትም ቢሆን ለቤተ ክርስቲያን እድገት ሴቶች ያልተሳተፉበት ትብብራቸውን ያላደረጉበት ጊዜ የለም ። በተለይም በሀገራችን አሁን ከሚታየው የሥልጣኔ ደረጃ አኳያ ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን በማስተባበር ባደረጉት ጥረት የጤና ጣቢያ ፤ የትምህርት ፤ የመንገድ ሥራ እና ሌሎችንም ችግሮች ለማቃለል ያስቻሉ ውጤቶችን ማስገኘታቸው ግልጽ ነው ።

በየአብያተ ክርስቲያናቱም በእህቶችና በወንድሞች ትብብር የታየው መልካም እንቅስቃሴ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናንን ችግር ብቻ ሣይሆን ቤ/ክ ትኩረት ለሰጠችው የእድገትና የልማት እቅዶች መሳካት ተጨማሪ ጥንካሬ አድርገዋል ። በዚህም የቀድሞዎቹን ቅዱሳት አንስት አርአያ የተከተሉ መሆናቸውን እንረዳለን ።

በጊዜያችንም ቅዱስ ሲኖዶስ ለቅድስት ቤ/ክርስቲያን እድገት የሚጠቅሙ የተለያዩ ደንቦችን በማውጣት ላይ ሲገኝ ከእነዚህ ደንቦች በቅድሚያ የሚጠቀሰው የምእመናንን ማኅበር ለማደራጀትና ለማጠናከር ብሎም ለማስፋፋት ተሻሽሎ የወጣው የሰበካ ጉባኤ ደንብ "ቃለአዋዲ" ነው ።

ይህ ደንብ መላዋ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.



www.ethiopianorthodox.org

በአንድ ዓይነት አስተዳደር በአንድ አመራር እንድትተባበር ወንድም ሆነ ሴት ታስቦ የወጣ ሲሆን ደንቡ ተፈጻሚነት እንዲኖረው የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት እንዳለው እና የጾታ ልዩነትም እንዳላደረገ ይታወቃል ። ቢሆንም በዘንድሮው ዘጠነኛ አጠቃላይ መንፈሳዊ ሰበካ ጉባኤ እንደታየው ከሆነ በጣት የሚቆጠሩ ሴቶች ብቻ ነበሩ የተሳተፉት እነዚህም ቢሆኑ የሰንበት ት/ቤትን ወክለው ከየሀገረ ስብከቱ የመጡ እንጂ ከሰበካ ጉባኤውማ ያለአንድም እህት አላየንም ።

ችግሩ ከምን ላይ ይሆን ? ከሰበካ ጉባኤ ወይስ ሴቶች "ሴት ልጅ ቀጥ ብላ ካየች አንገተ ሰባራ (አፋርም) ካልሆነች ባል አታገኝም" የሚለውን የቀድሞ አባባል ይዘው ለመሳተፍ ባለመፈለጋቸው ?

እንደሚገመተው ግን የየሀገረ ስብከቱም ሆነ የአ.አ ሰበካ ጉባኤ ሴቶችን በንዑስ ክፍልና በመስተዳድሩ እንዲሁም በአመራር ኮሚቴው የአባልነት ድርሻ የሰጣቸው ቢሆንም ከጉባኤው ላይ ያልተሳተፉበት ምክንያት ምን ይሆን ?

ይህንን አይተን በዝምታ አላለፍነውም ከየሀገረ ስብከቱ የመጡ አንዳንድ ሥራ አሥኪያጆችንና ተወካዮችን ጠይቀን እንደተረዳነው የሚከተለውን መልስ ሰጥተውናል።

"በእርግጥ እንደተባለው የመምረጥም ሆነ የመመረጥ እድል ቤ/ክ. ለሴቶች ሰጥታቸዋለች ይሁን እንጂ የልማድ ይሁን የባሕል ተጽእኖ አይታወቅም ለሰበካ ጉባኤ አባል ሆኖ ለመመረጥ ከወንዶች እኩል ምረጡን ብለው ሲቀርቡ አላየንም ይሁንና በዶክትሬት በዲግሪና በዲፕሎማ ተመርቀው በመንግሥት ሥራ በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ያሉ እህቶችና እናቶች እንዳሉ ቢታወቅም በመምረጡ እንጂ በመመረጡ እድል ቤ/ክርስቲያን የሰጠቻቸውን መብት አልተጠቀሙበትም በአባልነት ግን ተመዝግበው ማኅበር ደግሶ ካህናትን መመገብ ያስደስታቸዋል ። እንዲያውም ከመመረጡ ይልቅ መስበ ወርቅ ሰፍቶ ፡ መጋረጃ ፈትሎ ለቤ/ክርስቲያን ብጽአት ማበርከት ፡ ጧፍ እጣን ሻማ ገዝቶ መስጠት ፡ በቤት ያለውን አበርክቶ አጣፍጦ ማቅረብ እንግዳ በፈገግታ ተቀብሎ ማስተናገድና መሸኘት ፡ ልጅ ወልዶ ተንከባክቦ ማሰደግ እና ሌሎችንም የቤት አያያዝ የተመለከቱ ሁኔታዎች ማከናወን እጅግ በጣም ደስ ይላቸዋል ። ሲሉ ሐሳባቸውን ገልጸውልናል።

ለነገሩማ "የቃለ አዋዲውን" ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ ሲባል እንኳ የቅዱሳት አንስትን መንፈሳዊ አገልግሎት በሚገባ ያስተማሩ የንስሐ አባቶች ቢኖሩ ፈቃደኛ ባለመሆን በቤት ውስጥ ሥራ ይወሰኑ ነበር ? ለመልሱ የሶቅራጥስን አነጋገር እንመልከት ።

"አንዲት ሴት የግሪክ መምህራን ፊደል ሲያስቆጥራትና የሀገሪቷን ሕግና ሥርዓት ሲያስጠኗት ሴትየዋም የፊደል አቆጣጠሩ ሲገባትና ለመምህራኑ ጥሩ ጥሩ ጥያቄ ስታቀርብ አየ ። በብልህነቷ ተደንቆ "ይህችን ምላጭ የምትስሏት ማንን ልትላጩባት ነው አለ ይባላል ።

እንዳለውም ሴቶች ካሳዩዋቸው ካስተማሯቸው ልባምና አስተዋይ በመሆናቸው ሁሉ ነገር ሊገባቸው ስለሚችልና ፈጥኖ የመቀበል ችሎታ ያላቸው በመሆኑ አንደበታቸው ምላጭ ሆኖ የተማሩትን በማዳረስ ምጥፎውንና አጉሉን ባህል ከኅብረተሰቡ ላጭተው እንደሚጥሉት ከሶቅራጥስ አነጋገር መረዳት ይቻላል ።

ስለዚህ ከላይ የቀረበውን መልስ ተገን (ምክንያት) በማድረግ ሣይሆን ቤ/ክርስቲያን ዘወትር ሳትሰለች እንዲህ ያሉትን ሴቶች መሳልና ማስተማር ወደእርሷም እንዲቀርቡ ማድረግ ዓላማዋ ሊሆን ይገባል ።

በተለይም የየሀገረ ስብከቱም ሆነ የአ.አ. የሰበካ ጉባኤ ይህንን ዓቢይ ነገር አስቦበት ለአሥረኛው አጠቃላዩ መንፈሳዊ ሰበካ ጉባኤ ሴቶችን ለተሳትፎ እንደሚጋብዝ በስብሰባውም እንደሚገኙ ተስፋ እናደርጋለን ይህንም ስንል ያለሴቶች ተሳትፎ ቤ/ክርስቲያን ልታድግ ወንጌል ሊስፋፋ ምእመናንም ሊበዙ እንደማይችሉ በመተማመን ነው ።

መዓዛ አስማማው



## ዜና ዕረፍት


### የመልእክ ጽባሕ ውብነህ ዓባይ አጭር የሕይወት ታሪክ

መልአከ ጽባሕ ውብነህ ዓባይ ከአባታቸው አለቃ ዓባይ ከእናታቸው ወ/ሮ አካሉ ደስታ መጋቢት ፳ ቀን ፲፰፻፺፯ ዓ/ም ደቡብ ጎንደር ደ/ታቦር ሀ/ስብከት በእስቴ አውራጃ ጥናፋ ገነተ ጽጌ መሐልጌ ጊዮርጊስ ተወለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በተወለዱበት ደብር ከታላቅ ወንድማቸው መሪጌታ ላቀው ዓባይ ከፊደል እስከ ጸዋትወ ዜማ ተማሩ ከዚያ በኋላ ወደዋሻ ማርያም ሄደው ከመሪጌታ ገብረ ማርያም ጾመ ድጓና የዘወትር ምዕራፍ ተማሩ ።

ከዚያም በመቀጠል ወደ ስማዳ ሄደው መንደር ጊዮርጊስ ከመሪጌታ ምሥራቅ ዘመርሐ ቤቴ ለቤተ ክርስቲያናችን በር ከፋች የሆነውን ቅኔ ከእነ አገባቡ አጠናቀው ተማሩ ቀጥሎም የዲቁናን ሥልጣን ከአቡነ አብርሃም ተቀብለዋል ።

ከዚያ በኋላ በአባትና እናታቸው ፈቃድ በሥርዓተ ተክሊል ወ ሮ ስመኝ መሰሉን አግብተው ስድስት ሴቶች አምስት ወንዶች በድምሩ አስራ አንድ ልጆችን ሲወልዱ ከእነርሱም መካከል አንደኛው መሪጌታ ገብረ ኢየሱስ ውብነህ በሞት ከዚህ ዓለም የተለዩ ሲሆኑ ቄስ ገበዝ መንግሥቱ ውብነህ ና ቄስ ሳሙኤል ውብነህ የተባሉት ምሁራን ልጆቻቸው ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ላይ ይገኛሉ ።

መልአከ ጽባሕ ፡ ውብነህ ዓባይ ለቤተ ክርስቲያናችን ያበረከቱት አገልግሎት ያደረጉት የገንዘብና የጉልበት አስተዋጽኦ እጅግ ከፍ ያለ ነው ለማስረጃ ያህል ጥቂት እንጠቅሳለን ። አጋማች ኢየሱስ የተባለው ቤተ ክርስቲያን በዕድሜ ብዛት ስለፈረሰ እኒሁ አባት ደንጊያ በመጥረብ ጭቃ በማቡካት የፈረሰውን ቤተ ክርስቲያን በዘመናዊ መልክ አሳድሰው ታቦተ ሕጉ ከመቃኞ ወደ ታደሰው ቤተ ክርስቲያን እንዲገባ አድርገ


መልአከ ጽባሕ ውብነህ ዓባይ እኒህ ነበሩ

ዋል ።

የቤተ ክርስቲያኑን ሕንፃ ዕድሳት የተረዱት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ደብሩን ደብረ ጽባሕ ብለው ሠይመው እርሳቸውንም መልአከ ጽባሕ ውብነህ ዓባይ ብለው የደብሩ አስተዳዳሪ አድርገው ሹመዋቸዋል መልአከ ጽባሕ ውብነህ ስለቸኝ ታከተኝ ደከመኝ ሳይሉ ቤተ ክርስቲያን ፣ የሚያገለግሉ የተጣሉትን የሚያስታርቁ የተበደሉትን የሚያስክሱ ሰውን አክባሪ እግዚአብሔርን ፈሪ እውነተኛ ካህን ነበሩ እኒህ ሊቅ ጊዜያቸውን ሁሉ በተቀደሰ ተግባር ለማዋል የተዘጋጁ አባት ስለሆኑ በትንሹም በትልቁም በወንዱም በሴቱም ዘንድ ተወዳጅነት ነበራቸው ።

መልአከ ጽባሕ ውብነህ በመልካም ሥራቸውና አካሄዳቸው ለሁሉም አርዓያነት ያላቸው ነበሩ ከሕፃንነታቸው ጀምረው እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተለዩበት ጊዜ አልነበረም ምንም መልካም ሥራ ቢሠሩ ሥጋ ለለበሰ ሁሉ ሞት የማይቀር ዕዳ በመሆኑ በተወለዱ በ፹፫ ዓመታቸው የካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ተወልደው በአደጉበት ቤተ ክርስቲያን ወዳጅ ዘመድ ጎረቤት በርከት ያሉ ሊቃውንት በተገኙበት የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ።

ሥጋ ለለበሰ ሁሉ ሞት አይቀርም ሞት አለመቅረቱን የተገነዘቡ ሰዎች ሁሉ መልካም ሥራ ሠርተው ስለሚያልፉ መልካም ሥራቸው ተከታይ ትውልድን ሲያስተምር ይኖራል ። በመልአከ ጽባሕ መልካም ሥራ ተጠቅመው ቤተ ክርስቲያንን የሚያድሱና የሚሠሩ የሚያገለግሉ ፍቅርን ትሕትናን ራሳቸው ይዘውና ሠርተው ለሌላው የሚያሳዩ ሁሉ ዋጋቸው በመንግሥተ ሰማይ እንደሚቆያቸው ሊያውቁና ሊረዱ ይገባል ።

እንግዲህ ሁላችንም በሚያልፈው ዓለም የማያልፍ መልካም ሥራ ለመሥራት እንደ መልአከ



www.ethiopianorthodox.org

ጽባህ ውብነህ እንበርታ ።

የመልአከ ጽባህ ውብነህ ዓባይ ንም ቤተ ሰብእ ቸሩ ፈጣሪያችን ከነዘናቸው ያጽናናቸው ፡ ነፍሳቸ ውንም በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ ቃል ኪዳን በምትወረስ መንግሥተ ሰማይ ያሳርፍልን ዘንድ ወደ አምላካችን እንጸልያለን ።

የዜናው አቅራቢ
መሠረት ላቀው

---

# መሠረተ ሕይወት ማርያም

ታኅሣሥ ፫ ቀን በየዓመቱ በአታ ለማርያም እያልን የምናከብረው የሕይወት መሠረት የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበት ዕለት ነው ።

የሕይወት መሠረት የተባለችበትም ዋናው ምክንያት የመጀመሪያው ሰው ከተፈጠረ በኋላ እግዚአብሔር እሱን ብቻውን እንዲኖር ፈቃዱ ስላልነበረ ከግራ ጐኑ አንዲት አጥንት አንሥቶ ሴትን ፈጠረለት እሱም ከግራ ጐኑ የተፈጠረችውን ሴት ሄዋን ብሎ ጠራት ሔዋን ማለትም የሕያዋን እናት ማለት ነው ይህ ብቻ አይደለም በመቤታችን አማካይነት ሕይወት እንደሚያገኝና በእስዋም ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ሚዋሐድ ስለ ተገለጸለት ሔዋንን ሕይወቱ ናት ሲል ትንቢት ተናግሮ ነበር ።

ታድያ ይህም አልቀረም አዳም ከተፈጠረ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተሳሳተ የፈጣሪውን ትእዛዝ አፍርሶ የተደነገገውንም ሕግ ጥሶ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የጠነከረ ግንኙነት ተቋረጠ ።

በዚህም ምክንያት ለኃጢአት ተገዥ ሆነ ኃጢአቱ ከእሱ አልፎ ወደ ልጅ ልጁ ተላለፈ በተወለዱትም ልጆቹ ሁሉ ተዛመተ አዳም ይህንን የኃጢአት በሽታ በተያዘ ጊዜ በደሉን አውቆ ተጸጸተ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለውም አለቀሰ እግዚአብሔርም የምሕረት ባለቤት በመሆኑ ንሥሐውን አይቶ ጸጸቱን ተመልክቶ አንድ ታላቅ የሕይወትን ተስፋ ሰጠው የሰጠውም ተስፋ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ የሚል ነበር።

በሰጠውም ተስፋ መሠረት ከልጅ ልጅህ የሚለው ታላቅ ተስፋ ተፈጽሞ እመቤታችን ከልጅ ልጆቹ ከኢያቄምና ከሐና ተወለደች እመቤታችንም በተነገረላት ትንቢት እንጂ እንዲሁ በድንገት የተገኘች ወይም ሳትታወቅ የተገኘች አይደለችም ።

እመቤታችን ገና ሳትወለድ አባትዋ ዳዊት ትንቢት ተናግሮላት ነበር ትንቢቱም እስመ ሐረያ እግዚአብሔር ለጽዮን ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም ዝየ አሐድር እስመ ሐረይክዋ ።

እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወደዋታልና መርጫታለሁና ለዘለ ዓለም ማደሪያየ ናት ብሏል ።

ታድያ ይህ ቃለ ትንቢት ሲወርድ ሲዋረድ ከእመቤታችን ደረሰና ከኢያቄምና ከሐና ተወለደች ኢያቄምና ሐናም ሲወልድዋት በስለት ስለ ነበር በተወለደች በሶስት ዓመትዋ ስለታቸውን በማስታወስ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ወስደው ስለታቸውን አስረከቡ ።

ይህም ራሱ በትንቢት ሲነገር የነበረና የእስራኤል ሕዝብ ሲያነቡት የነበረ ነው ቃለ ትንቢቱም እበውዕ ቤተከ ምስለ መባዕየ ወእሁብ ብጽአትየ ዘነበብኩ በአፉየ "መባየን ይዤ ወደ ቤትህ አገባለሁ ስለት እሰጣለሁ ብየ በአፌ በተናገርኩበትም መሠረት ስለቴን እሰጣለሁ መዝ.፷፭ ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በትንቢተ ነቢያት ስትነገር የነበረች ከመሆንዋም በላይ በምሳሌም ስትወሳ ኑራለች ለምሳሌ ነቢዩ ኢሳይያስ በ፲፩ ም ቁ ፩ ላይ ትወጽእ በትር እምሥረወ እሴይ ወየአርግ ጽጌ እምኒኒሁ ብሏል ።

ይኸውም በትር ያላት እመቤታችንን ሲሆን ጽጌ ያለውም ከመቤታችን የሚወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያመለክተናል ።

በዚህ ዓይነት ትንቢትና ምሳሌ የተወለደችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንሆ በተወለደች ልክ በሦስት ዓመትዋ በወላጆቻዋ በኢያቄምና በሐና አማካይነት ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበት በስለት የተበረከተችበትና ስለትሁና ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠችበት ዕለት ነው ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ ልትገባ የቻለችው ፩ኛ/ ልማደ አንስት የሌለባት ንጽሕት በመሆንዋ

፪ኛ/ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባትና ከዚህ ሁሉ የተለየች ስለሆነች ፫ኛ/ ከኪሩቤልና ከሱራፌል ይልቅ የሚበልጥ ግርማ ያላት ስለሆነችና ከፍጡራን በላይ ከአንድ ከእግዚአብሔር በስተቀር ከእርስዋ ጋር በንጽሕና እና በቅድስና ተወዳዳሪ ስለሌላት ነው ።

ከእስዋ በፊት የነበሩ የአዳም ልጆች ሁሉ በኃጢአት ገመድ የታሠሩ በጎም ቢሠሩ ክፉውንም ቢሠሩ ሁሉም የሞት ተገዥዎች ነበሩ ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እለሂ አበሱ ወእለሂ ኢአበሱ ቀነዮሙ ሞት የበደሉትንም ያልበደሉትንም ሞት ገዛቸው ለማለት የቻለው ከዚህ የተነሣ ነው ሮሜ ፭፡ ፲፰ ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከመላእክት በላይ የመፈራት ግርማ አላት ስለዚህም ቅዱስ ኤፍሬም ከኪሩቤል ከመላእክት እስዋ ትበልጣለች ከሱራፌልም ትበልጣለች ምክንያቱም ከሶስት አካላት ለአንዱ ማደሪያ ሁናለችና ሲል ጽፎላታል ።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም ከሴቶች ሁሉ ትበልጫለሽ ሲል ያመሰገናት ያለ ምክንያት አልነበረም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ሀገረ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆንዋን በመገንዘቡ ነው ።

እንግዲህ ቅዱሳን መላእክት የሚያመሰግንዋትና የሚሰግዱላት ቅዱሳን መላእክት የምትበላውንና የምትጠጣውን እያመጡ የሚላኩትና የሚያገለግሏት በንጽሕና እና በቅድስና የተለየች ንጽሕት ዘር ናት ምክንያቱም ዓለም ሳይፈጠር በሕሊና አምላክ የነበረች ናትና ።

እንዲያውም እንደ ሌሎቹ ከአዳም የወረደ የኃጢአት ውርስ እንደ ሌለባት ሲያስገነዝብ ወኢረኩስት በምንትኒ እምዘፈወራ ከፈጠራት ጀምሮ ምንም አልተለወጠችም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስም የለባትም ሲል በምንትኒ በማለት ታሪክ ይምድሞት ይገኛል ።

ከአዳም የወረደው የጭንት አበሳ ኃጢአት በሰው ልጆች እንደ ነበር ደጋጎች ሰዎችም ሳይቀሩ በዚህ ተይዘው እንደነበር የሃይማኖት መጽሐፍትን ይመሰክራል ነገር ግን የዚህ ዓይነት የኃጢአት ውርስ በእመቤታችን አለ ብሎ የሚያምን ወይም በእመቤታችንም አለ ብሎ የሚያስተምር በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን አልነበረም ዛሬም የለም ለወደፊትም አይኖርም ። ከፈጠራት ጀምሮ ለማደሪያው ስለ መረጣት ምንም አልተለወጠችምና ።

መሠረተ ሕይወት የተባለችውም ዋና ፍሬ ነገር መንገድና እውነት ሕይወትም እኔ ነኝ ያለውን የሕይወት መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእናትነት ስለ መረጣት ነው ።

እመቤታችን ወደ ቤተ መቅደስ ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ ፲፪ ዓመት ሙሉ በፋኑኤል አማካይነት ሰማያዊ ምግብን እንጂ ምድራዊውን ምግብ ተመግባ አታውቅም ።

አባሕርያቆስም ይህንን በማስመልከት ሰማያዊውን ኅብስት እንጂ ምድራዊውን ኅብስት አልተመገብሽም ሲል ጽፎ እናገኘዋለን ።

ስለዚህ በቤተ መቅደስ ውስጥ ፲፪ ዓመት ስትኖር ቅዱሳን መላእክት እያገለገልዋት በንጽሕና በቅድስና ኑራለች ።

በዚህም መሠረት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታኅሣሥ ፫ ቀን በየዓመቱ ስታከብራት ትኖራለች ።

ከነፊ ርግብ ማርቆስ





## ጸአተ እስ…

ከገጽ ፳ የዞረ

ማይ እያወረደ ሲመግባቸው ውሃ ከድንጋይ እያፈለቀ ሲያጠጣቸው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሙሴን ቃል በቃል እያነጋገረ ሲያሟላላቸውና ፡ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤልም ከአደጋ እየጠበቀ ሲመራቸው እምነታቸውን በእግዚአብሔር ብቻ አላደረጉም ፡ የሚደረጋላቸው ተአምርና ችሮታ አላረካቸውም ፡ ያው በግብፅ ሲያገኙት የነበረው የባዕድ ፍርፋሪ እየናፈቃቸው ሙሴን በዚህ በረሐ ልትፈጀን ነው? ከግብፅ ለምን አወጣኸን? እያሉ ያማርሩት ነበር ።

በዚህም ምክንያት ፵ ቀን የማይፈጅ ጉዳና ፵ ዓመት ፈጀባቸው ከግብፅ የወጡ ሽማግሌዎች ምድረ ርስትን ሳያዩ በዚሁ አለቁ ሙሴና አሮንም እንኳ ወደከነዓን አልገቡም" አሮን በ፩፻፳፫ ዓመቱ በሆር ተራራ ሙሴም በ፩፻፳ ዕድሜው በሞአብ ሜዳ ሞቱ ።

ደግ ሲሠሩለት ክፉ የሚያስብ ፡ ሲረዱት የማይረዳ ፡ ውለታቢስ ሰው ሲያጋጥመን እሱ ሰው አይደለም እንላለን በሰው ዘንድ እንኳ ይህን ያህል የሚያስከፋ ከሆነ የእግዚአብሔርን ውለታ የማናስብ ከሆነ ምን ያህል ጉዳት እንደሚያስከትል ከዚህ ታሪክ መማር ይገባል ።

በመጨረሻም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን በሙሴ ምትክ እያሱን ተከትላቸው በእርሱ መሪነት እስራኤል ወደሀገራቸው ከነዓን መግባት እንደቻሉ ታሪኩ በሰፊው ያብራራል ቅዱስ ጳውሎስ "እሳብህን ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ተው እሱ ይመግብሃል ።

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል

www.ethiopianorthodox.org

# የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት በቁልቢ

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ፊት የሚቆም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከታዘዘበት ቦታ የሚያደርስ ፈጣንና ተራዳኢ መልአክ ነው ።

እግዚአብሔር የለመነውን ሁሉ ለመፈጸም ቃል ገብቶለታል። ስለዚህ ለቅዱስ ገብርኤል መጋቢ ሐዲስ የሚል የቅጽል ስም ተሰጥቶታል ።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ስሙን ጠርቶ በስሙ ለሚማፀን በተቻለ ፈጥኖ የሚሰማ ተራዳኢ መልአክ ነው ። በሐረር ክፍለ ሀገር የሚገኘው ቁልቢ የተባለው ቦታ ፤ ታሪኩ እንደሚከተለው ተመዝግቧል ።

በቁልቢ የቅዱስ ገብርኤል ታቦት እንዲተከል የሆነበት ታሪኩ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው ።

በቅዱስ ገብርኤል ስም የተቀረጸ ታቦት በአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ይኖር ነበር በአክሱም ጽዮን ይኖሩ የነበሩ ታቦታትና ንዋየ ቅድሳት በጓጼ አንበሳ ውድም ትእዛዝ ወደዚይ መጥተው እንዲቀመጡ ሁኖ ነበር ። በኋላ ታቦታቱ ሁሉ ወደ አክሱም ሲመለሱ የቅዱስ ገብርኤል ታቦት በዚይ ይቀራል ። ስሙ አባ ሌዊ የተባለ የበቃ ባሕታዊ ወደ አክሱም ሄዶ አክሱም የነበረው ታቦተ ገብርኤል በዚይ ደሴት መኖሩን ለዓፄ አንበሳ ውድም ተናግሮ ታቦቱን ከዚይ ደሴት ወደ አክሱም ለማምጣት ዓፄ አንበሳ ውድምን ፈቃድ ይጠይቃል ። እርሳቸውም ይፈቅዱለትና ጉዞውን ተያይዞ ዚይ ደሴት በመድረስ ታቦተ ገብርኤልን ይዞ ወደ አክሱም ጽዮን ለመሔድ መንገድ ይጀምራል መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በራዕይ ተገልጾ ታቦተ ገብርኤልን እንደያዘ



ቅ·ገብርኤል ፫ቱ ደቂቅን ከእሳት እንዳዳናቸው

ቁልቢ ወደሚባለው ቦታ እንዲያመራ ይነግረዋል ። አባ ሌዊም እኔ የምወስደው ወደ አክሱም ጽዮን ነው ብሎ ክርክር ያደርጋል ።

መልአኩም አባ ሌዊ ሆይ! አሁን የማነጋግርህ ከእግዚአብሔር ፊት የምቆመው እኔ ገብርኤል ነኝ ። ስለዚህ ትእዛዜን አክብረህ አስተዳማ ወደ ነገርኩህ ቦታ ወደ ቁልቢ ሒድ ብሎ መንገዱን ይመራዋል ። አባ ሌዊም እየፈራና እየተንቀጠቀጠ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል መሪነት ቁልቢ ከሚባል ቦታ እንደደረሰ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለአባሌዊ እንዲህ አለው ። ወዳጄ ሌዊ ሆይ! ይህን ቦታ አስቀድሞ እግዚአብሔር የመረጠው በመሆኑ በእግዚአብሔር ፈቃድ እኔም ልዩ ልዩ ሥራ የምገልጽበት ታላቅ ቦታ ነው ። አንተም በዚህ ታርፋለህ ይህ በስሜ የተሰየመውም ታቦት ሥውር ሁኖ ይኖራል በዚህ ሥውር ሆኖ በሚኖረው ታቦትም ምትክ ሌላ በስሜ ታቦት ይተከል በታል ይህንን የነገርኩህንም ሁሉ ጽፈህ ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፍ አድርግ ብሎ ነግሮት መልአኩ ከፊቱ ተሠወረ አባ ሌዊ ይም የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራና የቅዱስ ገብርኤልን ኃይል በማድነቅ ለእግዚአብሔር ከፍ ያለ ምስጋና አቀረበ ። ከዚያ ወዲህ አባ ሌዊ በታቦተ ገብርኤል እየተማፀነ ከኖረ በኋላ ዋሻ ፈልፍሎ ታቦቱን በዚያ አስቀምጦ የቦታውን ታሪክና የራሱን ታሪክ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም የነገረውን ሁሉ በድንጋይ ላይ ጽፎ አርፏል ።

በአጼ ልብነ ድንግል ዘመን የታሪክ ተመራማሪዎች ቁልቢ ላይ ይደርሳሉ ።

በዚያ በቁልቢ አባሌዊ የጻፈው ጽሑፍ በታሪክ ተመራማሪዎች ይመዘገብና ጽሑፉም ተገልብጦ ተጽፎ በዚይ ደሴት ለመዘከር ይቀመጣል ።

ልዑል ራስ መኰንንም የቦታውን ሁኔታ ያጠናሉ በጥናቱም ከፍተኛ ምልክት ይገኝበታል ። በዚህ ምክንያት ልዑል ራስ መኰንን ታቦተ ገብርኤልን በቡልጋ አውራጃ አባ ዱብ አለ ከተባሉ መነኩሴ ካስመጡ በኋላ በዚህ በቁልቢ አንባ ላይ ቤተ መቅደስ አሠርተው ቅዱሴ ቤቱን ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ያከብራሉ

የቁልቢ ገብርኤልንም ቤተ ክርስቲያን ለመሳለም የሚጓዘው ሕዝበ ክርስቲያን እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ ከድሬዳዋ እስከ ቁልቢ ድረስ መንግሥት የአስፋልት መንገድ እንዲሠራ አድርጓል ይህ መንገድ በመሠራቱም ያልተደሰተ ምእመን አይገኝም በቁልቢ የቅዱስ ገብርኤል በዓለ ንግሥ የሚከበረው ታኅሣሥ ፲፱ ቀንና ሐምሌ ፲፱ ቀን ነው ። የቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ባጭሩ ይህን ይመስላል ፡ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ታሪክ የተገኘውም ከጸድቁ ከአባ ሌዊ ገድል ነው ገድሉ የሚገኘውም አዲስ አበባ ከተማ ኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲ ጥናትና ምርምር ክፍል ነው ።

እንባብያን ሆይ ኢትዮጵያ ሀገራችን ብዙ አስደናቂዎች የሆኑ የተአምር ቦታዎች አሏት ከብዙዎቹም አንዱ ይህ የቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ነው ። የተሳልነውን ለመስጠት ያልተሳልነውን ለመሳል ዘወትር በእግረ ልቡና ወደዚህ ቤተ ክርስቲያን እንገሥግስ እግዚአብሔርም በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል አድሮ ስለታችንን ይፈጽምልናል ።

የዜናው አቅራቢ አባ ገብረ መስቀል
ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም

# ጸአተ እስራኤል

እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘርህን እንደምድር አሸዋ እንደሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ ፡ በዘርህም አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ፡ ማርና ወተት የምታፈሰውን አገር ከንዓንን ለአንተና ለዘርህ እሰጣለሁ ፡ አንተም ቃል ኪዳኔን ትጠብቃለህ ብሎ በሰጠው ቃል መሠረት ልጁ እስራኤል የተባለ ያዕቆብ ከነልጆቹና ከነልጅ ልጆቹ በከነዓን ምድር በዝቶ ኖረ።

ነገር ግን ልጆቹ በወንድማቸው በዮሴፍ ላይ ክፉ ሥራ ሠሩ ይኸውም ዮሴፍን አባቱ ይወደው ስለ ነበርና ወደ ፊት የሚሆንውንም እግዚአብሔር በሕልም ገልጾለት ያየ ስለነበረ በምቀኝነት ተነሥተው ሲገድሉት አሰቡ ፡ ከወንድሞቹ አንዱ ይሁዳ ግን የወንድማችንን ደም በከንቱ ብናፈስ ምን ይጠቅመናል ብንሸጠው ይሻላል በማለት ለግብፅ ነጋዴዎች በ፳ ብር ሸጡት ዮሴፍም በግብፅ አገር ብዙ ፈተና ከደረሰበት በኋላ የንጉሡ ፈርዖንን ሕልም በመተርጎሙ ባለሟል ሆኖ ተሾመ ።

በምድርም ሁሉ ላይ ረሐብ ሆነ በተለይ ማርና ወተት ስታመነጭ በነበረችው ከነዓን ጸና ። በዚህም ምክንያት እሥራኤል ሰብአ ነፍስ ሆነው ወደ ግብፅ ተሰደዱ በዚያም ዮሴፍን አገኙት ። ዮሴፍም እንደ ጠሉኝ ልጥላቸው እንደበደሉኝ ልበድላቸው ሳይል በደስታ ተቀብሎ ከንጉሡ ፈርዖን አስተዋውቆ በእርሱ አማካይነት ለረኀቡ ዘመን ከተጠራቀመው እህል እየበሉና እየጠጡ እንዲኖሩ ፡ የሚሰፍሩበትም ቦታና ለመንጎቻቸው ማሰማሪያ እንዲሰጣቸው አደረገ። ከፋን በክፉ ፋንታ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ በዚህ ፈንታ ባርኩ እንጂ በረከትን ልትወርሱ ለዚህ ተመርጣችኋልና ፩ኛ ጴጥ ፫ – ፱

ከብዙ ዘመናትም በኋላ ዮሴፍና ፈርዖን ሲሞቱ እስራኤላውያንን የማያውቅ ሌላ ንጉሥ በነገሠ ጊዜ ግዞት አጸናባቸው ሥርዓት አክበደባቸው እየረቡና እየበዙም በሄዱ ቁጥር ግብፃውያን የጭቆናና





www.ethiopianorthodox.org

የግፍ አገዛዝ እያበዙባቸው ሄዱ ከዚህም ሌላ ከእሥራኤላውያን ሴቶች ወንድ ልጅ ሲወለድ እንዲ ገደል ስለታወጀ ማንኛውም ሕፃን ገና ከእናቱ ማኅፀን ሲወጣ ተገ ድሎ ወደ ባሕር ይጣል ነበር ።

እግዚአብሔርም ይህንን ግፍና በደል አይቶ ከወገኖቻቸው ሙሴና አሮንን አስነሣላቸው እነ ሱም እንደ:ታዘዙት ወደፈርዖን ቤት ገብተው "እግዚአብሔር ሕዝበ እስራኤልን ልቀቅ ይል ሃል" ቢሉት ጉልበታቸው ጥሞት ስለነበረ "እግዚአብሔርን አላው ቅም እስራኤልንም አልለቀም" አለ ።

እንዲያውም ከበፊቱ ይበልጥ እንዲሠሩ ጥብቅ ትእዛዝ አስተላ ለፈ ። ሥራውም ከአቅማቸው በላይ ሆኖ መሥራት ሲሳናቸው በፈርዖን ሹማምንት ይገረፋና ይረ ገጡ ጀመር ። ሙሴና አሮንንም እንዲህ ያለ መልእክት አምጥታ ችሁ ስቃይ አብዛችሁብን በማለት አማረሩ ፤ ሙሴና አሮንም ወደ እግዚአብሔር አመለከቱ ። ከዚ ህም በኋላ ያ ትዕቢት ጥፋትን ፤ የኩራት መንፈስም ውድቀትን ያስከትላሉ" እንደተባለው ግብፅ በተለያዩ ፲ መቅሰፍቶች ተመ ታች ፤

፩ኛ ውሆች ደም በመሆን
፪ኛ በጓጉንቸር
፫ኛ በቅማል
፬ኛ በዝንብ
፭ኛ በቸነፈር
፮ኛ በቁስል
፯ኛ በበረዶ
፰ኛ በአንበጣ
፱ኛ በ፫ቀን ጨለማ
፲ኛ በበኩር ልጅ ሞት

ይህ ሁሉ ሲሆን ፈርዖን ሊመ ለስ አልቻለም ። ልቡ ደንድኖ ነበርና ለጊዜው መቅሰፍቱን ሲያይ ሙሴና አሮን ወደ "እግዚአ ብሔር ጸልዩልኝ ይል ነበር በእነር ሱም ጸሎት መቅሰፍቱ ሲያቆም እንደገና አልለቅም" ይላል ።

ነገር ግን የመጨረሻው መቅሰ ፍት ከንጉሡ ቤት ጀምሮ የግብፃ ውያንን ሁሉ የበኩር ልጅ በሞት ስለቀጣ ፤ ግብፃውያን ጮሁ ፤ እስራኤል ከሀገራችን ይውጡ ልን" አሉ ፈርዖንም ለራሱ ስለ ፈራ እስራኤልን ለቀቀ ።

እግዚአብሔር ኃይልና ሥል ጣን በእጁ ሲሆን "በደለኞችን ወዲያው አያጠፋም ብዙ ጊዜ ይታገሳል ርኅሩኅና መሐሪ ነው ከቁጣ የራቀ ምሕረቱም የበዛ ነው" (መዝ ፩፻፵፭ — ፰ ለማይመ ለሱና ለማይጸጸቱ ግን ኃይሉ ይገ ልጽባቸዋል" ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ ይደቅቃሉ በሰማ ይም ያንጐደጉድባቸዋል እርሱ እስከምድር ዳርቻ ይፈርዳል ፩ኛ ሳሙ ፪ — ፲

ከዚህም በኋላ በሙሴ መሪነት በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት በሌ ሊት ተነሥተው ወጡ በዚህም ቀን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረቡ ይህም ዕለት የደስታ ቀን በመሆኑ ፋሲካ ተብሎ በየዓመቱ እስከልጅ ልጅ እንዲያከብሩት ተደርጓል ዘጸ ፲፪—፵፫ ግብፃውያ ንም በእስራኤል መውጣት ደስ አላቸው ፈርተዋቸዋልና (መዝ. ፩፻፬ — ፴፰) ስለዚህ የእስራኤል ከግብፅ ባርነት ነፃ መውጣት "ጸአተ እስራኤል" የተባለው የቅ ዱስ ሚካኤልንም በዓል ኅዳር ፲፪ ቀን በየዓመቱ የምናከብረው በእ ርሱ ተራዳኢነት የእስራኤልን ከግብፅ መውጣት መታሰቢያ በማ ድረግ ነው ።

እስራኤላውያን በራብ ምክን ያት ራሳቸው ወደው ግብፅ በመኖ ራቸው መብታቸውን ማስከበር አልቻሉም "በባዕድ ቢቆጡ ፤ በጨለማ ቢያፈጡ እንደሚባለው ፬፻፴ ዓመታት ሙሉ በግብፃው ያን የመረረ አገዛዝ ተገዙ ነገር ግን እግዚአብሔር ስለራራላቸው በረቀቀ ጥበቡ ወደ ሀገራቸው እን ዲመለሱ አሰባቸው ።

ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደ መና እየጋረደ መራቸው ፈርዖን ግን ያ ሁሉ መቅሰፍት ተረስቶት እንደገና ከነሠራዊቱ ተከተላቸው ኤርትራ ባሕር በደረሱ ጊዜ እግዚ አብሔር ሙሴን አለው "በትርህን አንሣ እጅህንም በባሕሩ ላይ ዘርጋ ሙሴም እንዲሁ አደረገ ባሕሩም ግራና ቀኝ ተከፈለ ፤ እስራኤልም በደረቅ ተሻገሩ ፈርዖን ከነሠራዊ ቱና ሰረገሎቻቸው ከባሕሩ መካ ከል እንደደረሱ ሙሴ እንደገና እጁን ወደ ባሕር ቢዘረጋ ግራና ቀኝ እንደግድግዳ ሆኖ ቆሞ የነበ ረው ባሕር ገጠመ ግብፃውያንንም በዚያው ሰጠመ ።

በኃይሉ ብርታት ፤ በሠራዊቱ ብዛት ተመክቶ እስራኤልን ለዘለ ዓለም አገልጋይ አድርጎ ለመኖር ያለው ፍቅር የጸና ስለሆነ መቅሰፍ ቱና ቅጣቱ ሊመልሰው አልቻለም ስለዚህ መቃብሩ በአሸዋ ውስጥ ሆኖ ቀረ እስራኤላውያንም የጠላ ቶቻቸውን በፊታቸው መውደቅ የእነርሱንም በደረቅ መሻገር በማ የታቸው ይህንን ተአምር ላደረገላ ቸውና ታላቅ ውለታ ለዋለላቸው አምላክ" ንሴብሖ ለእግዚአብ ሔር ሰቡሐ ዘተሰብሐ በማለት የምስጋና መዝሙር አቀረቡ ።

ሕዝቡ እስራኤል እግዚአብ ሔር የሚወዳቸውንና የሚጠበቃቸ ውን ያህል እነሱም ሕጉን አልጠ በቁም ትእዛዙን አላከበሩምና ከሰ

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



# "ብርሃን ወደ ዓለም መጣ"

በዓለም ውስጥ ብዙ የተለያዩ የብርሃን ዓይነቶች አሉ ፤ ከእነዚ ህም አንዱና ግዙፉ ብርሃን ፀሐይ ነው ፤ እግዚአብሔር አምላክ ይህ ትልቅ ብርሃን በቀን እንዲሰለጥን፣ ጨረቃና ከዋከብትም በሌሊት እንዲሰለጥኑ አድርጓል ።

ከነዚህም በቀር ሰው ሠራሽ ብርሃናት አሉ ፤ እነዚህም ከትልቁ የኤሌክትሪክ ብርሃን እስከ ኩራዝ ያሉት ናቸው ፤ የሰው ልጅ በእው ቀት ከመራቀቁ በፊት ከክትክታ ቅጥቅጥ መብራት ተነሥቶ እስከ ፋኖስ መብራት ድረስ ይጠቀም እንደነበረና ከጥቂት ዓመታት በፊት ደግሞ ከፋኖስ ተነሥቶ እስከ ማሾ ፤ ከዚያም እስከ ኤሌክ ትሪክ መብራት ለመራመድ (ለማ ደግ) መቻሉን እንገነዘባለን።

በመሠረቱ ብርሃን ምንድር ነው? ለምንስ ተፈጠረ? ብለን ብን ጠይቅ እግዚአብሔር አምላክ ብር ሃንን የፈጠረበት ዋና ምክንያት ጨለማን (ለማስወገድ) ለማራቅ ነው ። ጨለማ የጥፋት ምልክት ሲሆን ብርሃን ደግሞ የልማትና የሕይወት ዋስትና ነው ። በመሆ ኑም ብርሃን የጨለማ ተቃራኒ ነው ።

ጨለማ የብዙ ነገር ምሳሌ ነው ፤ ይኸውም አንዱ በሌሊት የሰለጠነው ጨለማ ሲሆን ሁለተ ኛው ድንቁርና ነው ፤ ይህም በጨ ለማ ይመሰላል ፤ አለማስተዋልም የጨለማ ጓደኛ መሆኑን ሊቃው ንት ይተረጉማሉ ፤ ከአባቶች አንዱ ኢዮብ "እኛ ከጨለማ የተ ነሣ በሥርዓት መናገር አንችል ምና የምንለውን አስታውቀን" ብሎ አል (ኢዮ.፴፯ — ፲፱) የሰው ክፋትም በጨለማ ተመስሎአል ቅዱስ ጳውሎስ በበኩሉ ስለዚሁ ጉዳይ ሲያመሠጥር በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን ዕውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባ ችን ውስጥ የበራ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና ፤ ፪ኛ.ቆሮ.፬ — ፮ ሲል በክፋት ጨለማ የተሸፈነው ልባችን ክርስ ቶስን በማወቅ ይገለጥ ዘንድ እንዲ ገባ ያስገነዝባል ።

በሌላው መልኩም ጨለማ የኩ ነኔ ምሳሌ መሆኑን ያመለክታል ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠው ምሳሌያዊ ትም ህርት "በዚያን ጊዜ ንጉሡ አገል ጋዮቹን እጁንና እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አው ጡት በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋ ጨት ይሆናል" (ማቴ ፳፪ — ፲፫) የሚል ነው ፤ ከዚህ በላይ የብርሃ ናት ዓይነትና መጠን የጨለማ ትርጉም አባባል በመጠኑ ተብራ ርቶአል ነገር ግን አተኩረን የምን መለከተው ቁም ነገር ጨለማ በብ ርሃን ሲወገድ እንጂ ጨለማ ብርሃ ንን እንደማያስወግደው በሁሉም ዘንድ የተረጋገጠ ነው የቤ/ክርስ ቲያን መምህራንና ሊቃውንት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በብርሃን ዲያብሎስን በጨለማ መስለው ያስተምራሉ ፤ ደግሞም ብርሃንን በእውነተኛ ፍርድ ጨለማን በተሳሳተ ፍርድ የሚያነፃጽሩ አሉ ።

በተጨማሪም ያለእምነት የሚ ኖር (ዓለም) ሕዝብ በጨለማ ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማ መን ሕጉን በመፈጸም የሚኖሩ ምእመናንና መኖሪያቸውንም በመንግሥተ ሰማያት እያነፃጸሩ እንደሚያስተምሩ እንሰማለን ።

ሰዎች ያለእምነት የሚኖሩበት ዓለም በጨለማ ከተመሰለ ለዚህ ቦታ የማይጠፋ ብርሃን እንደሚያ ስፈልገው የታመነ ነው ስለዚህ እግዚአብሔር በጨለማ ተው ጠው ለሚኖሩ ሰዎች ብርሃን ሰደ ደላቸው ነቢዩ ኢሳይያስ "በጨ ለማ የሄደ (የሚኖር) ሕዝብ ብር ሃን አየ በሞት ጥላ አገርም ለሚ ኖሩ ብርሃን ወጣላቸው" ብሎአል (ኢሳ.፱ — ፪) ጨለማ የሚለው ስም ይህ የምናየው ከቀን ብርሃን ጋር የሚፈራረቀው ሁሉም የሚያ ውቀው ጨለማ ሳይሆን የሃሳብ ፤ የሕሊናና የልብ ጥመትን የሚያስ ከትል ነው ክፉ ግብርም የሚመነ ጨው ከዲያብሎስና ከእኩያን አጋንንት ነው እግዚአብሔር አም ላካችን ሰዎችን ከማፍቀሩ የተነሣ በዲያብሎስና በአጋንንቱ በጨለ መው ዓለም ለተዋጡት አንድ ልጁን ወደዚህ ዓለም ላከታል ።

ወንጌላዊው ዮሐንስ "በመጀ መሪያ ቃል ነበር ቃልም በእግዚአ ብሔር ዘንድ ነበረ ፤ ቃልም እግዚ አብሔር ነበረ ካለ በኋላ በእርሱ ሕይወት ነበረች ፤ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች ብርሃንም በጨለማ ያበራል ጨለማም አላሸ ነፈውም" (ዮሐ.፩ — ፩ — ፭) ሲል አገናዝቦ ጽፎአል ቃልና ብርሃን የተባለው ወልደ እጓለ እምሕያው ክርስቶስ ነው ነገር ግን ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓ ለም ብርሃን ሆኖ በጨለማ (በአጋ ንንት አገዛዝ) ያሉትን የሰው ልጆች ብርሃኑን ሊያዩ በራሳቸው ከድንቁርና ጨለማ ከክፉ ሀሳብና ምኞት ከምቀኝነትና ከተንኰል



www.ethiopianorthodox.org

ነፃ አውጥቶ ወደ ሕይወት ጐዳና ሊመራቸው ቢመጣ አልተቀበሉትም አልተከተሉትም ።

ስለዚህም ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን ወደ ዓለም ስለመጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው ፤ ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን (ክርስቶስ) አይመጣም" ሲል ተናግሯል (ዮሐ. ፫ – ፲፱ – ፳፩) በሌላም በኩል ወንጌላዊው ዮሐንስ በመልእክቱ እግዚአብሔር ብርሃን እንደሆነ ሲመሰክር" ከእርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወራላችሁ መልእክት እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም" እንዲሁ በእግዚአብሔር ዙሪያ ከብርሃን በስተቀር የጨለማ ምልክት ምንስ (እንኳ ከቶ እንደሌለ ብርሃኑን የቀመሰ ወንጌላዊ ቅዱስ ዮሐንስ ከዚህ በኋላ በሰጠው ትምህርት አስገንዝቦናል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የብርሃኑ ተካፋይ ከመሆኑ የተነሣ ስለብርሃኑ ጥቅም ሲያስረዳን እርሱ ብቻ የማይሞት ነው ፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያየውም አይችልም" ይላል ቃሉን ለተቀበሉ እርሱን ለተከተሉ በእምነት እንደሚያዩት ቅዱስ ጳውሎስ ለልጁ ለጢሞቴዎስ ሲያስረዳ በየጊዜውና በየዘመኑ የሚወለዱ አዳማውያን ሁሉም እግዚአብሔርን (ክርስቶስ) በእምነት ለማየት እንደሚችሉ ያስረዳዋል (፩ኛ/ጢሞ. ፮ – ፲፮ ፤ ፩ኛ ዮሐ.፩ – ፭)

በተጨማሪም የእግዚአብሔር ሕግ ብርሃን ነው በሕጉ የሚኖሩ በሕጉ የሚመሩ ሁሉ በብርሃን ይመላለሳሉ ሕግጋቱን አውቆና ጠንቅቆ የኖረው ቅዱስ ዳዊት" ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው" በማለት የዘመረውን እናነባለን ። (መዝ. ፩፻፲፰ – ፩፻፲፭)

ጨለማ ማለት የሰው ልጆች ድንቁርና አለማስተዋል ፤ ክፋት የኩነኔ ሁኔታም መሆኑን ከዚህ በላይ አንበናል እግዚአብሔር ብርሃን መፈጠሩን ራሱ እግዚአብሔር ብርሃን መሆኑን የገለጸው አንድ ልጁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነኝ ብሎ መመስከሩንና ማስተማሩን ብርሃኑም በሰዎች ልብ እንደሚያበራና ሕጉንም በብርሃን መመስሉንና በክርስቶስ ብርሃንነት ያመኑ ምእመናንም የዓለም ብርሃን መባላቸውን (ማቴ.፭ – ፲፬ – ፲፮) ካወቅንና ከተረዳን ዘንድ ከዛሬ ጀምሮ ወይም ቃሉን ከሰማንበት ሰዓት እንሥቶ በክርስቶስ ብርሃናዊ መንገድ መጓዝ እንደሚገባን መረዳት አለብን ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል እስከ ቤተ ልሔም እየተመሩ የሄዱት በኮከብ ብርሃን ነው ። በዚያች በተወለደባት ሌሊትም ቤተ ልሔም ብርሃን ተሞልታ እንዳደረች የተረጋገጠ ነው ። ይኸውም እነሆ የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ" ይላል የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጌትነቱ ብርሃን በሁሉም ዘንድ ታውቆአል በብርሃን ውስጥ የሚኖር እውነተኛ ብርሃን መሆኑንና ለሰዎችም ብርሃን የሚያድል መሆኑን ሲያረጋግጥልንም" እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል" በጨለማ አይመላለስም "ብሎአል"

ስለዚህ ሁላችንም ይህንን በጨለማ የሚያበራውን የዓለም ብርሃን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በንጹሕ ልብና በእውነተኛ እምነት መከተል አለብን ከእርሱ ጋር መኖር በሕጉ መመላለስ ሕጉን መፈጸምና መጠበቅም ወደዘለዓለማዊ ሕይወት የሚያስገባ የዘለዓለም ደኅንነት የሚገኝበት የሕይወት ብርሃን ነውና በብርሃኑ እንድንመላለስ ይፈቅድልን ዘንድ ወደ ዓለም የመጣው የማይጠፋው የዘለዓለም ብርሃን እንዲያበራልን የተቀደሰ ፈቃዱ ይሁንልን ።

ሊ/ትጉሃን ገ ክርስቶስ ኃ ማርያም

## ጸአተ እስ…

ከገጽ ፲፯ የዞረ

እንዳለው እነርሱም አሳባቸውን በአምላካቸው ብቻ ጥለው ትእዛዙን አክብረው ቢለምኑት ኖሮ ይህን ያህል ዘመን በስደት ባልኖሩም ነበር ምክንያቱም እግዚአብሔር እንኳንስ ከልብ ለምነውት እየበደሉት እንኳን አልተዋቸውም ከግብፅ ግዛት ነፃ አውጥቶ ወደሀገራቸው አግብቶአቸዋል ።

ስለዚህ ሁላችንም ከሚደርስብን ፈተና ሁሉ መልአኩን ቶሎ ልኮ እንዲያወጣን ያለማማረር በንጹሕ ልብ እሱን መከተል አለብን ።

መ/መንክር ዋሴ



# ታላቁ የእግዚአብሔር ቀን

ታላቁ የእግዚአብሔር ቀን የተባለው ነቢያት ትንቢት ሲናገሩለት ዘመን ሲቆጠርለት የኖረውና ከአሁን ቀደም ተደርጎ የማያውቅ ወደፊትም ሊደረግ የማይችል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ የሰላም ቀን ነው የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ የራቁትን የሚያቀርብ የቀረቡትን የሚያበረታታ ለሰው ልጅ የተስፋ መድኅን የሚሆን አንድ ሕፃን በቤተልሔም ተወለደ ። እሱም ክርስቶስ ነው ። በዚሁም ስፍራ እረኞች ነበሩ ። እነዚህም በሜዳ መንጋቸውን እየጠበቁ በሌሊትም እየተጉ ነበር ። ሳይታሰብ ድንገት የእግዚአብሔር መልአክ በአጠገባቸው ቆመ ብርሃንም በዙሪያቸው በራ በዚህ ጊዜ ፈሩ መልአኩም አትፍሩ አላቸው ቀጥሎም ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ደስታና የመስራች እነግራችኋለሁ ዛሬ መድኅን ተወልዶላችኋል እሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይህም ምልክት ይህ ሁሉ ሲሆን ብዙ የሰማይ መላእክት ከመልአኩ ጋር ነበሩ ሰውና መላእክትም በመሬት አንድ ሆነው ለእግዚአብሔር ክብር በአርያም ፤ ሰላምም በምድር ለሰው ልጅ ፈቃድ ይሁን እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ (ሉቃስ.፪.፰ – ፲፬) የእግዚአብሔር ታላቁ ቀንም የተባለው በዚህ ምክንያት ነው ።

ሰብአ ሰገልም በኮከብ ብርሃን እየተመሩ ወደ ተወለደው ሕፃን ይጓዙ ነበር ። በምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው ነበር ። ሕፃኑንም ባዩ ጊዜ እጅግ ደስ አላቸው ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አግኝተው ሰገዱለት ሳጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት (ማቴ. ፪ – ፱ – ፲፩)

እነዚህ ምሥራቃውያን ወርቅ፥ ዕጣንና ፤ ከርቤ ብቻ ሳይሆን በጉዞአቸው የደከሙትን ድካም በፀሐይ ግለት በአሸዋ እረመጫ ፤ የፈሰሰውን ላባቸውንና ንጹሕ ልባቸውን ጭምር ለእግዚአብሔር የተወደደና ጣፋጭ መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ ። ለምሳሌ እንዲት ልጃገረድ ከአባቷ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው በምሽት ሲንሸራሸሩ ሳለ በሰማዩ ላይ የሚያበሩ ወይም የሚያብረቀርቁ ከዋክብት ተመለከተች በታላቅ ደስታ ተነክታ "ሰማይ የተዋበ ነው" አለች አባቷም ልምን እንዳሰበች ቢጠይቃት በወለሉ ዘልቆ የሚታየው የከዋክብት ብርሃን ያማረ ስለሆነ ነው ስትል መለሰችለት አባትየውም የምሥራቅ ሰዎችን ክርስቶስ ወደተወለደበት ወደ ቤተልሔም እየመራ ይዟቸው የመጣው ኮከብ ከእነዚህ አንዱ ነው አንቺም እንደ ምሥራቅ ሰዎች በነዚህ ከዋክብት እየተመራሽ ብትሄጂ ክርስቶስን ታገኝዋለሽ ልብሽንም ንጹሕ አድርገሽ ክርስቶስ እንደተወለደበት ቤተልሔም ብታደርጊው ክርስቶስ በፀጋው በምሕረቱ ይጐበኝሻል ሰላምም ይሰጥሻል አላት ። ይኸውም ሰማይ የእግዚአብሔር መቀመጫ ዙፋን ስለሆነ እና የሠራውም ሥራ ሁሉ የሚገለፅበት በመሆኑ ልብሽም የእግዚአብሔር ዙፋን እንዲሆን ማማር አለበት ሲል አስረዳት ልጅቷም ልቧን ለማሳመር ተዘጋጀች ነገር ግን ይህ ከፍጥረት በኋላ በኃጢአት ያለንበት ምድር የመጀመሪያው ሰው የመጀመሪያይቱ ሴት እስከበደሉ ድረስ እጅግ በጣም ውብ ነበር ። ይኸውም ምድር መጀመሪያ ሲፈጠር ምን ያህል መልካም እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን ይህንንም ለማወቅ ቢፈለግ እራሱ እግዚአብሔር አምላካችን ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆ እጅግ መልካም ነበር እንዳለ እናገኛለን። (ዘፍ.፩ – ፴፩)

ይህም የሆነው በሰው ልጆችና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ግንኙነት በመቋረጡ ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ምክንያት ሞት በሰው ልጆች ላይ ነገሠ ክርስቶስ ተወልዶ ለሰው ልጆች ሰላምን እስኪሰጥ ድረስ ሰውና ምድር የከፋውን የኃጢአት ወረራ ሊቋቋሙት አልቻሉም ነበር ። ስለዚህ ምድርም ተበላሸች ሰውም ተዋረደ ። የኃጢአትም ሸክም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከበደ በመሄዱ ምድርም ከገነትነት ወደ ገሃነምነት እየተለወጠች ሄደች ። ስለዚህም ነቢዩ ኢሳይያስ ምድርም እንደልብስ ታረጃለች የሚኖሩበትም እንዲሁ ይሞታሉ ማዳኔ ግን ለዘለዓለም ይሆናል ጽድቄ አይፈርስም ብሏል (ኢሳ.፶፩ – ፮) እንደተነበየውም ምድር በኃጢአት ብትረክስና ብታረጅም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በልደቱ አደሳት የሰው ልጅ ቢዋረድም በልደቱ ከፍ ከፍ አድርጐ አከበረው በመንፈሱም በፀጋውም ከሁሉም አላቀው በመንፈስም የሞቱት በልደቱ ለዘለዓለም ሕያው ሆነው ይኖራሉ በክርስቶስ ልደት የተገኘውም ጽድቅ እራሱ ሳይፈ



www.ethiopianorthodox.org

ርስ ኃጢአትን እያፈረሰና ሕሙማንን እየፈወሰ ፀንቶ ይኖራል ሕሙማንም በልደቱ ሕይወትንና ደኅንነትን እንዳገኙ ይመሰክራሉ ።

ለምሳሌ ነቢዩ ኤልሳዕ በእስራኤል ራብ ፀንቶ በነበረበት ዘመን ነገ ጥጋብ ይሆናል ብሎ ተናገረ በዚያን ዘመን የነበረው ንጉሥ ግን እነሆ እግዚአብሔር በሰማይ መስኮቶች ቢያደርግ ይህ ነገር ይሆናልን? ሲል መለሰለት ኤልሳዕም መልሶ በዓይኖችህ ታየዋለህ



ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ እንስሳት በትንፋሻቸው እንዳሟሟቁት

ነገር ግን አትቀምስም ስላለው ያየውን እህል ሳይቀምስ ሞቷል ። በዚሁ በረሃብ ዘመን የሚኖሩ አራት ለምፃሞች ነበሩ ከዚህ ብን ቀመጥ በረሃብ እንሞታለን ወደ ከተማም መግባት ብንወድ በከተማም ረሃብ አለ በዚያም እንመታለን እንግዲህ ወደ ሶርያውያን ከተማ በሕይወት ቢያኖሩን እንኖራለን ቢገድሉንም እንሞታለን ተባባሉ ጨለምለም ሲል ወደ ሶርያውያን ከተማ ገቡ ሶርያውያንም በጨለማ ሸሽተው ስለነበር በከተማው ማንም አልነበረም ንብረታቸውን ሀብታቸውን የተከሉትን ድንኳን ጥለው ሸሽተው ነበርና እንዚህም ለምፃሞች በየድንኳኑ እየገቡ ተርበው ነበርና በሉ ጠጡ ጠገቡም ከዚያም ወርቅና ልብስ ብርም ወስደው ሸሸጉ በጥቂት ጊዜም ሀብታሞች ሆኑ ከዚያም ወዲያ እርስ በእርሳቸው መልካም አላደረግንም ዛሬ የመልካም ምሥራች ቀን ነው እኛ ዝም ብለናል እስኪነጋም ድረስ ብንቆይ በደለኞች እንሆናለን ተባብለው ሄደው ለንጉሡ ቤተሰቦች ተናገሩ (፪ኛ ነገሥት·ም· ፯·፩—፲፪)

ከቃሉ እንደተረዳነው እኛ በልተን ጠጥተን ከጠገብን በየአይነቱ ልብስ አግኝተን ከለበስን ወርቅና ብር አግኝተን ከከበርን ሌላው ቢራብና ቢጠማ ሌላው ልብስ አጥቶ ቢራቆት ገንዘብ አጥቶ ቢደኸይ ምን ቸገረኝ ብለው አልተቀመጡም ዛሬ የምሥራች ቀን ስለሆነ የተራቡት ወገኖቻቸው እንዲጠግቡ የታረዙት እንዲለብሱ የደኸዩት እንደ እነሱ እንዲከብሩ ከቦታው ሄደው ሀብት እንዲያገኙ ብለው ለወገኖቻቸው ሁሉ ነግረዋል ። ወገኖቻቸውም በነገሯቸው መሠረት ወደ ቦታው ሄደው ከረሃብ ከችግር ድነው ብዙ ሃብት አግኝተው ከብረዋል

ዛሬም የወንጌል መምህራን የሆንን ሁሉ በከተማም ሆነ በገጠር ለሚኖሩ ወገኖቻችን ቅዱስ ቃሉን የሚነግራቸው ስለአጡ የመንፈስ ረሃብ ይራባሉ የመንፈስ ሀብትና መንፈሳዊ ፀጋ አግኝተው እንዲከብሩ ክርስቶስ የተወለደበትን ቤተልሔምን የሚያሟያቸውና በክርስቶስ የተገኘውን ሰላም ዛሬ የምስራች ቀን ነው ብሎ የሚነገራቸው በማጣት ይንከራተታሉ ።

ስለዚህ ክርስቶስ እንደተወለደባት ቤተልሔም በእነሱ ልብ ክርስቶስ እንዲወለድ ማስተማር ይኖርብናል ። በተጨማሪም ያ የእስራኤል ንጉሥ እህሉን አይቶ ሳይቀምሰው እንደሞተ ከንባቡ የተረዳን ይመስለኛል ዛሬም አማኞች የሆኑ ሁሉ በሃይማኖት ፀንተው በምግባር በርትተው በዓይናቸው ያዩትንና በቤተልሔም የተወለደውን የኢየሱስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ሳይቀምሱ እንዳይሞቱ መምህራን ማስተማር ይገባናል ካልተማሩ እውቀት ካልቆረቡ ደኅንነት አይገኝምና ልደቱን እየተዘዋወርን እናስተምር ላልሰሙትም እናሰማ ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በተገ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቍ·
የመልእክት ሣ·ቍ· 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org